# የዕዝራና የነህምያ

# መጻሕፍት መክፈቻ

## ለመሠረታዊ ደረጃ

## ሁለተኛ ዓመት

አንደኛ እትም 1977 ዓ.ም.
ሁለተኛ እትም 1981 ዓ.ም.
ሦስተኛ እትም 1984 ዓ.ም.

# መቅድም

መክፈቻ የተሰኙት መጻሕፍት በተለይም መጽሐፍ ቅዱስን ገና ላልተማሩት ሰዎች የተቀናበሩ ናቸው። የመጻሕፍት ዋና ዓላማ የየመጽሐፉን ይዘት በአጭሩ መግለጥ ነው። በመሆኑም ዓላማው እንደ ጥናት፣ ማብራሪያ ወይም ትርጓሜ አይደለም። ይህ መጽሐፍ የእግዚአብሔርን ቃል የመክፈት ዓላማ ስላለው ተማሪዎች የተለያዩትን ትምህርቶች ሳያጠኑ እንደሚያልፉ የታወቀ ነው፤ መጽሐፉ እያንዳንዱን እንቀጽ ለማብራራት አይሞክርም፤ የታሪኩን አሻሚ ክፍሎችን በሙሉ ለመተርጐም ዓላማው አይደለም። ነገር ግን ተማሪዎች በዚህ መክፈቻ ተመርኩዘው ቢያጠኑ የእግዚአብሔርን ቃል ሲያነቡ ይረዱታል፤ በግልጽና በደስታ ሊያስተምሩት ይችላሉ።

አዘጋጆች

# ማውጫ

ገጽ

ክፍል አንድ ዕዝራ 1-2 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1
ክፍል ሁለት ዕዝራ 3-6 . . . . . . . . . . . . . . . . . . 8
ክፍል ሦስት ዕዝራ 7-10 . . . . . . . . . . . . . . . . . . 14
ክፍል አራት ነህምያ 1-2 . . . . . . . . . . . . . . . . 19
ክፍል አምስት ነህምያ 3-7 . . . . . . . . . . . . . . . 24
ክፍል ስድስት ነህምያ 8-10 . . . . . . . . . . . . . . 29
ክፍል ሰባት ነህምያ 11-13 . . . . . . . . . . . . . . . 33
መልሶች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 42-46

# ክፍል አንድ የእስራኤላውያን የመጀመሪያው ምርኮ መልስ ዕዝራ 1-2

## የዕዝራ 1-2 ታሪካዊ አቀማመጥ

### የእስራኤላውያን ወደ ምርኮ መወሰድ

እስራኤላውያን ትዕዛዙን ባይጠብቁ እንደሚቀጣቸው እግዚአብሔር ለብዙ ዓመታት አስጠንቅቋቸው ነበር። ግዛታቸውም በሰሜናዊና በደቡባዊ ግዛቶች የተከፈለ ነበር። ሰሜናዊው የእስራኤል ግዛት መጀመሪያ ተሸነፈ። ሰማሪያ ተይዛ ሕዝቢም ወደ አሶር ተወሰደ፤ 2ኛ ነገሥ. 18፡9-12። ከመቶ ሠላሳ ዓመታት በኋላ ደቡባዊው ግዛት በናቡከደነፆር ተያዘ። ሕዝቡም ተይዞ ወደ ባቢሎን ተወሰደ፤ 2ኛ ነገሥ. 25።




### የኤርምያስ ትንቢት

ኢየሩሳሌምና ቤተ መቅደሱ ሲፈራርሱና እስራኤላውያን ወደ ባቢሎን ሲወሰዱ ኤርምያስ ትንቢት ተናገረ። ሰባ ዓመት ባቢሎን ውስጥ ከቆያችሁ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ትመለሳላችሁ፤ ኤር.25፡12። ዳንኤል የኤርምያስን ትንቢት ሲያነብ የመመለሳቸው ወቅት የተቃረበ መሆኑን ተገነዘበ፤ ዳን.8፡1። ዓመቱ ከማለቁ በፊት ባቢሎን በፋርሱ ንጉሥ በቂሮስ ተያዘች።

### የእስራኤላውያን ወደ አገራቸው መመለስ

ኤርምያስ እንደተነበየው ከሰባዎቹ ዓመታት በኋላ ቂሮስ ፈቃደኛ የሆነ እስራኤላዊ ሁሉ ወደ ኢየሩሳሌም መመለስ እንደሚችል አስታወቀ፤ 2ኛ ዜና 36፡22-33። አንዳንድ የሸመገሉ እስራኤላውያን አገራቸውን አስተውሰው ለመመለስ ጓጉተው ነበር። ብዙ ወጣት እስራኤላውያን ግን ቤታቸውን በባቢሎን ውስጥ መሥርተው ነበር። ምንም እንኳን ብዙዎች ለመመለስ ባይፈልጉም እግዚአብሔር ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ ልባቸውን አነሣሣ፤ ዕዝራ 1፡5።

### የኢየሩሳሌምና የቤተ መቅደሱ ፍርስራሽ

ኢየሩሳሌምና ቤተ መቅደሷ ፈራርሰው ነበር። ቤተ መቅደሱ ተቃጥሎ ነበር። የከተማዎቹ ቅጥሮች ፈራርሰዋል። ቤተ መቅደስ ውስጥ የነበሩት የወርቅና የብር ሰሐኖች ሁሉ ተወሰዱ፤ 2ኛ ዜና 36፡15-21።

## የዕዝራ 1-2 መግቢያ አስተያየቶች

ጊዜው ሲደርስ እግዚአብሔር የፋርሱ ንጉሥ ቂሮስ እስራኤላውያን ወደ አገራቸው እንዲመለሱ አዋጅ እንዲነገር ልቡን አነሣሣ። በፋርስ ግዛት ያሉት እስራኤላውያን ሁሉ ወደ ኢየሩሳሌም ለመመለስ ተዘጋጁ። የይሁዳና የብንያም ጐሣ አለቆች ይህንኑ ለመፈጸም የመጀመሪያዎቹ ነበሩ። ካህናትና ሌዋውያንም አብረዋቸው ሆኑ።

የይሁዳ ልዑል ዘሩባቤል ወደ እስራኤል ለሚመለሱት የመጀመሪያው ቡድን መሪ ነበር። ኢያሱ የቡድኑ ካህን ሆነ። በዘሩባቤል፥ በኢያሱና በዘጠኝ ሌላ ሰዎች መሪነት ተማርከው የነበሩት እስራኤላውያን ወደ ኢየሩሳሌም አመሩ።

## የዕዝራ ታሪክ 1-2

### የቂሮስ አዋጅ

በመጀመሪያው ዘመነ መንግሥቱ ቂሮስ ለፋርስ ግዛት አዋጅ አወጀ። አዋጁም «የሰማይ አምላክ እግዚአብሔር በይሁዳ ባለችው በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ እንድሠራለት አዘኛል። ማንም የእግዚአብሔር ሰው ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ቤተ መቅደሱን መሥራት ይችላል። እግዚአብሔርም ከርሱ ጋር ይሁን። ወደዚያም ለሚሄደው ጐረቤት የሆነ ሁሉ በብር፥ በወርቅ፥ በዕቃዎችና በእንስሳት መርዳት አለበት። እንዲሁም በኢየሩሳሌም ለሚሠራው ቤተ መቅደስ እያንዳንዱ ሰው አቅም በፈቀደ መጠን ይስጥ» ይላል፤ ዕዝራ 1፡1-4።

### ቤተ መቅደስ ውስጥ የነበሩት ሰሐኖች መመለስ

እግዚአብሔር የይሁዳና የብንያም ጐሣ አለቆችን ልብ አነሣሣና ለመሄድ ተዘጋጁ። ንጉሡ እንዳዘዘው በአቅራቢያቸው ያሉትም ረዷቸው። ናቡከደናፆር የወሰደባቸውን ንብረት ቂሮስም



መለሰላቸው። የወርቅና የብር ሰሐኖች በአጠቃላይ 5400 የወርቅና የብር ዕቃዎች ቂሮስ ወደ ኢየሩሳሌም መለሰ፤ ዕዝራ 1፡5-11።

### ከዘሩባቤል ጋር የተመለሰው ቡድን

ወደ አገራቸው የሚመለሱትን የመጀመሪያዎቹን ዘሩባቤልና ኢያሱ መሩ። እያንዳንዱ ሰው ከራሱ ቤተሰብ ጋር ተመድቦ ነበር። ካህናት፥ ሌዋውያን፥ መዘመራን፥ ጠባቂዎችና የቤተ መቅደስ ሠራተኞች ሁሉ ተመዝግበው ነበር። ኢየሩሳሌም እንደደረሱ አንዳንዶች በፈቃደኝነት ለቤተ መቅደሱ እርዳታ አደረጉ። እነርሱም ወርቅ፥ ብርና ለካህናቱ ልብስ እንደ ችሎታቸው አቀረቡ። በከተሞቻቸውም በይሁዳ ውስጥ ሠፈሩ። የተመለሱትም ሰዎች ወደ 50000 ይጠጋሉ፤ ዕዝራ 2፡1-70።

## ከዕዝራ 1-2 የወጡ ጥያቄዎች

1. ቂሮስ በእግዚአብሔር የሚያምን ንጉሥ ነበር?

መልስ:- አልነበረም። ቂሮስ በብዙ አማልክት የሚያምን ንጉሥ ነበር።

2. የማያምኑ መሪዎች ፈቃዱን እንዲያከናውኑ እግዚአብሔር በሥልጣኑ ሊጠቀምባቸው ይችላል?

መልስ:- አዎን። እግዚአብሔር እስራኤላውያን ወደ አገራቸው እንዲመለሱ የቂሮስን ልብ አነሣሣ፤ ምሳሌ 21፡1 እና መዝ. 75፡6-7።

3. ከ70 ዓመት በኋላ እስራኤላውያን ወደ አገራቸው እንደሚመለሱ ኤርምያስ እንዴት አወቀ?

መልስ:- እውነተኛ የእግዚአብሔር ነቢይ የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራል። ስለዚህ ኤርምያስ ትክክል ያልሆነ ትንቢት ሊተነብይ አይችልም። በዘዳግም 13፡1-5 እና 18፡20-22 ውስጥ የእውነተኛ ነቢይን ብቃት እናገኛለን።

## የማይለወጥ የእግዚአብሔር ቃል ዕዝራ 1-2

### እግዚአብሔር ይወስናል

እግዚአብሔር በቂሮስ ዘመን እንደ ነበረው አሁንም ተቆጣጣሪ አምላክ ነው። እግዚአብሔር አሁንም መሾምና መሻር ይችላል። ስለዚህ የእኛ ኃላፊነት ከእኛ በላይ ያሉትን ማክበርና ከእግዚአብሔር የተሰጠንን ትዕዛዝ መፈጸም ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ «ሥልጣን ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፤ እያንዳንዱ ሰው ከበላዩ ላሉት ይገዛ» ብሏል፤ ሮሜ 13፡1። ሐዋርያው ጴጥሮስ እንዲህ ብሏል:-

«ስለ ጌታ ብላችሁ ለበላዮቻችሁ ተገዙ።» 1ኛ ጴጥ. 2፡13-14።

### የእውነተኛ ነቢይ ምልክቶች

ብሉይ ኪዳን ላይ እንዳሉት ነቢያት እውነተኛ አስተማሪዎች የእግዚአብሔርን ቃል ያስተምራሉ። ከሐሰተኛ ነቢያት እንድንጠነቀቅ ተነግሮናል፤ 1ኛ ጢሞ. 1፡6-7። የሚያስተምሩትን መፈተንና በሐሰተኛ ነቢያት መታለል የለብንም፤ 2ኛ ጢሞ. 4፡1፤ 1ኛ ጢሞ. 1፡7 እና 2ኛ ጴጥ. 2፡1።

## ማጠቃለያ

እስራኤላውያን በጣዖት ማምለካቸውን ከቀጠሉ እንደሚቀጣቸው እግዚአብሔር ለብዙ ዓመታት አስጠንቅቆአቸው ነበር። ትዕዛዙን ባለመጠበቃቸው ኢየሩሳሌምና ቤተ መቅደሷ በጠላት እንዲፈራርሱ እግዚአብሔር አደረገ። ሕዝቡም በግዞት ወደ ባቢሎንና አሶር ተወሰደ።

እግዚአብሔር ሕዝቡን አልረሳም፤ ነቢዩ ኤርምያስ ከሰባ ዓመት በኋላ ወደ አገራቸው እንደሚመለሱ ተነበየ። ጣዖት አምልኮ በነበረባቸው በባቢሎንና በአሶር እስራኤላውያን የጣዖት አምልኩአቸውን አቆሙ። ጊዜው ሲደርስ እግዚአብሔር ቂሮስን አስነሣ። ቂሮስም ማንኛውም ወደ አገሩ መመለስ የሚፈልግ እስራኤላዊ መመለስ እንደሚችል አሳወቀ። ቂሮስ እስራኤላውያን እንዲመለሱ ከማደፋፈሩም ሌላ ሌሎች በገንዘብና በዕቃ እንዲረዷቸው አዘዘ።

የይሁዳ ልዑል ዘሩባቤል የመጀመሪያውን ቡድን የመራ ነበር። የተመለሱት 50000 የሚሆኑ ሰዎች ነበሩ። ለቤተ መቅደሱ ሥጦታ ከሰጡ በኋላ በየመንደሮቻቸው ሠፈሩ።

## ጥያቄዎች ዕዝራ 1-2

1. እስራኤላውያን ከአገራቸው ወደ ሩቅ አገር የተወሰዱት ለምንድነው?
2. ከእስራኤላውያን ግዛቶች መጀመሪያ የተያዘው የትኛው ነበር? በግዞት ወዴት ተወሰዱ?
3. የደቡባዊው ግዛት ሕዝብ ወዴት ተወሰደ?
4. ኢየሩሳሌምና ቤተ መቅደሱ ምን ደረሰባቸው?
5. እስራኤላውያን በግዞት የሚቆዩበትን ጊዜ የተነበየው ማን ነው? በምርኮ የሚቆዩት ለምን ያህል ጊዜ ነበር?
6. ቂሮስ ማን ነው? በእግዚአብሔር ያምን ነበር?
7. እስራኤላውያን ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ቂሮስ እንዲያሳውቅ ያደረገው ማን ነው?
8. እስራኤላውያን ኢየሩሳሌም ውስጥ ምን ሊያደርጉ ነበር?
9. ቂሮስ በቢሎን ውስጥ ለቀሩት የሰጠው ትዕዛዝ ምንድነው?
10. ቂሮስ ለእስራኤላውያን የመለሰው ምንድነው?



# ክፍል ሁለት የቤተ መቅደሱ መገንባትና መመረቅ

## የዕዝራ 3-6 ታሪካዊ አቀማመጥ

### ከምርኮ በኋላ የተነበዩ ነቢያት

ዘሩባቤል የመጀመሪያዎቹን እስራኤላውያን ወደ ኢየሩሳሌም በመራ ጊዜ ሐጌና ዘካርያስ ነቢያት ነበሩ። የተወለዱትም በሰባዎቹ የግዞት ዓመታት በባቢሎን ውስጥ ላይሆን አይቀርም። እስራኤላዊያን ወደ አገራቸው ሲመለሱ አብረዋቸው ተመለሱ፤ ዕዝራ 5፡1። ስብከታቸውና ትምህርታቸው ለእስራኤላውያን ማበረታቻ ነበር።

### የቤተ መቅደሱ ግንባታ

በዘሩባቤል የሚመሩት እስራኤላውያን ኢየሩሳሌም በገቡ በሰባተኛው ወር ቤተ መቅደሱን መሥራት ጀመሩ። ይሁንና በተቃውሞ ምክንያት እስከ አሥራ ስድስት ዓመት ድረስ ሥራው አላለቀም ነበር።

### የፋርስ ነገሥታት

በቂሮስና በአርጤክስስ እስከ ዳርዮስ ዘመነ መንግሥት ድረስ እስራኤላውያን ከፋርስ ነገሥታት ብዙ ቅራኔዎች ነበሩአቸው። ይህ ቅራኔ የቤተ መቅደሱ ሥራ እንዲቆም አድርጎታል።

## የዕዝራ 3-6 መግቢያ አስተያየቶች

### ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱት እስራኤላውያን

በባቢሎን የነበሩት እስራኤላውያን ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ ንጉሥ ቂሮስ ፈቅዶላቸውና አበረታቷቸው ነበር። ምንም እንኳን በሰማርያ የነበሩት ባለሥልጣኖች ቢቃወሟቸውም እስራኤላውያን ወደ አገራቸው ተመለሱ። ባለሥልጣኖቹ በተለያዩ መንገዶች የቤተ መቅደሱን ግንባታ ሊያደናቅፉ ሞከሩ። ይህም ቅራኔ ከቂሮስ ዘመነ መንግሥት እስከ ዳርዮስ ዘመነ መንግሥት ድረስ ለአሥራ ስድስት ዓመታት ቀጥሏል፤ ዕዝራ 4፡4-5።

### በባቢሎን የቀሩት እስራኤላውያን

ወደ አገራቸው ሳላተመለሱት እስራኤላውያን የተጻፈው በጣም ጥቂት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ የተገኘው መረጃ በዚያን ጊዜ በባቢሎን የሆነው የአስቴር ታሪክ ብቻ ነው። በአስቴር

ጊዜ ጨከበሰ የባቢሎን ንጉሥ ነበር። በባቢሎን የነበሩት እስራኤላውያን ይነቀፉና ይቀጡ ነበር። የአስቴርን ታሪክ አንብብ።

# የዕዝራ 3-6 ታሪክ

## አምልኮ በኢየሩሳሌም እንደገና ተጀመረ

በሰባተኛው ወር መጨረሻ እስራኤላውያን በየከተሞቻቸውና በየመንደሮቻቸው እንደገና ሠፈሩ። ቤታቸውን ከመሠረቱ በኋላ በኢየሩሳሌም ተሰብስበው የእግዚአብሔርን መሠውያ መሥራት ጀመሩ። በሙሴ ትዕዛዝ መሠረት የሚቃጠል መሥዋዕት ለእግዚአብሔር አቀረቡ። የምሽትና የንጋት መሥዋዕቶችን ማቅረብ ጀመሩ። የዳስ በዓልም አደረጉ። በየቀኑ የሚገባውን መሥዋዕት አቀረቡ፤ ዕዝራ 3፡1-6።

## የቤተ መቅደሱ ግንባታ ተጀመረ

እስራኤላውያን የሚቃጠሉ መሥዋዕቶችን በማቅረብ እግዚአብሔርን ካመሰገኑ በኋላ ለቤተ መቅደሱ ሥጦታ ማምጣት ጀመሩ። የምግብ፥ የመጠጥና የዘይት ሥጦታዎች ከሊባኖስ በሚመጣው በዝግባ እንጨት ምትክ ወደ ጢሮስ እና ወደ ሲዶና ተላኩ። ከተመለሱ ከአሥራ አራት ወራት በኋላ አይሁዶች ቤተ መቅደሱን መሥራት ጀመሩ። የተመለሱት ሁሉ በሚሠሩበት ጊዜ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ በሥራው ተካፋይ ሆኑ፤ ዕዝራ 3፡7-13።

## ቤተ መቅደሱ እንዳይሠራ የነበረው ተቃውሞ

የእስራኤላውያን ጠላቶች ቤተ መቅደሱ እየተገነባ መሆኑን ሰሙ። ወደ ዘሩባቤል ዘንድም መጥተው «ቤተ መቅደሱን በመገንባት እንርዳችሁ» አሉት። ነገር ግን ዘሩባቤልና ኢያሱ ጠላቶች መሆናቸውንና ሥራውን ሊያደናቅፉ እንደሆነ ስላወቁ እርዳታቸውን ተቃወሙ። ሕዝቡም እስራኤላውያንን ለማስፈራራትና ከሥራቸው ለማገድ መሞከራቸውን ቀጠሉ።

ቤተ መቅደሱ እንዳይገነባ የነበረው ቅራኔ ለ16 ዓመታት ቀጠለ። በአርጤክስስ ዘመነ መንግሥት የይሁዳና የብንያም ጠላቶች የሐሰት ክስ ደብዳቤ ላኩለት። በአርጤክስስ ዘመነ መንግሥት ጠላቶቻቸው እስራኤላውያን ሽፍቶች ሆኑ ብለው ከሰሷቸው። ንጉሡም ሥራው መቆም እንዳለበት ትዕዛዝ አስተላለፈ። እስከ ዳርዮስ መንግሥት እስከ ሁለት ዓመት ሥራው ቆመ፤ ዕዝራ 4ን አንብብ።

## የቤተ መቅደሱ ሥራ ቀጠለ

ነቢያት የነበሩት ሐጌና ዘካርያስ ኢየሩሳሌምና ይሁዳ ውስጥ ለሚኖሩት እስራኤላውያን ትንቢት ተናገሩ። ዘሩባቤልና ኢያሱ መልዕክታቸውን ሲሰሙ የተቋረጠውን ሥራ ለመሥራት ተነሣሡ። «ሆኖም መንግሥቱ ቤተ መቅደሱን ለመሥራት ማን ፈቀደላችሁ?» ብለው ጠየቋቸው። እግዚአብሔር ግን የአይሁድ መሪዎችን ይጠብቅ ነበር። አይሁዳውያን ሁሉ ምን እንደሚሠሩ ጠላቶቻቸው ለንጉሥ ዳርዮስ አሳወቁ። ንጉሥ ዳርዮስ መዛግብትን ሲመረምር



የቂሮስን አዋጅ አገኘ፤ ስለዚህ ዳርዮስ የቂሮስን ትዕዛዝ ደግፎ የይሁዳን ሹማምንቶች በሥራው እንዲረዱ እንጂ እንዳይከለክሉ አዘዛቸው። የሚያስፈልገውን ሁሉ እንዲሰጡ ታዘዙ። የቀረጥ ገንዘብን ለዕርዳታው ተጠቀሙ። ስንዴ፥ ጨውና የወይን ጠጅ ለመሥዋዕትነት ለሚቀርቡት እንስሳት መስጠትም ነበረባቸው። ይኸውም የሰማይ አምላክ ዳርዮስንና ልጆቹን እንዲባርክ ነበር። ዳርዮስ ማንም ለመርዳት የሚቃወም እንደሚገደል ቤቱም እንደሚፈርስ ተናገረ፤ ዕዝራ 5፡1-6፡12 አንብብ።

## የቤተ መቅደስ መመረቅ

ሹማምንቱ እንደ ዳርዮስ ትዕዛዝ ይሠሩ ነበር። አይሁዳውያንም በነቢዩ ሐጌና በነቢዩ ዘካርያስ አበረታችነት የቤተ መቅደሱን ሥራ ጨረሱ። ካህናቱ፥ ሌዋውያንና ከምርኮ የተመለሱት ሁሉ የእግዚአብሔርን ቤት ቅዳሴ መረቁ። በዚህም ለእግዚአብሔር በመቶ የሚቆጠሩ መሥዋዕት አቀረቡ። ካህናቱንና ሌዋውያንንም ለቤተ መቅደሱ አገልግሎት አደራጁ።

## ፋሲካ

አይሁዳውያን በግዞት በነበሩት ዓመታት የፋሲካን በዓል አላከበሩም። የቤተ መቅደሱ ሥራ ካለቀ በኋላ ካህናቱና ሌዋውያን ራሳቸውን አንጽተው እንስሳትን ለፋሲካው በዓል መሥዋዕት እንዲሆኑ አረዱ። ከባቢሎን የተመለሱትና የአረማኔ ተግባራቸውን የተዉ ሁሉ መሥዋዕት እያቀረቡ እግዚአብሔርን ማምለክ ጀመሩ። የቂጣውንም በዓል ለሰባት ቀናት አከበሩ። የፋርሱ ንጉሥ በሥራቸው ስለረዳቸው እግዚአብሔርን አመሰገኑ።

# ዕዝራ 3-6ን የሚመለከቱ ጥያቄዎች

1. በዚያን ጊዜ በፋርስ ግዛት ውስጥ ስንት ነገሥታት ነበሩ?

| ሁኔታው | ቀን | ንጉሥ | የተጠቀሱ መጻሕፍት |
|---|---|---|---|
| ዘሩባቤል ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሰውን የመጀመሪያውን ቡድን መራ። | 536 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት | ቂሮስ | ዕዝራ 1 |
| አይሁዳውያን ቤተ መቅደሱን መሥራት ጀመሩ። | 534 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት | ካምቢሲስ | ዕዝራ 4:3 |
| የቤተ መቅደሱ ግንባታ ቀጠለ። | 520 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት | ዳርዮስ 1 | ዕዝራ 4:5 እና 24፤ 5:6 እና 6:7 |
| የቤተ መቅደሱ ሥራ አለቀ። | 516 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት | | ዕዝራ 6:15 |
| | 486 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት | ጤክስስ | የአስቴር ታሪክ |
| ዕዝራ ሁለተኛውን ቡድን መራ። | 486 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት | አርጤክስ | ዕዝራ 7:1 |



2. በነገሥታቱ ስም ላይ የስም መደናገር ያለው ለምንድነው?

መልስ፡- አይሁድ ውስጥ በነበሩት ሹማምንትና በፋርስ ነገሥታት መካከል የነበረው ስምምነት ተመዝግቧል። እነዚህ ደብዳቤዎች በዚያን ጊዜ ይፋ በነበረው በአራም ቋንቋ ተጽፈዋል። ብዙው የብሉይ ኪዳን የተጻፈው በእብራይስጥ ነበር፤ ዕዝራ 4:6-23። የጤክስስ እና የአርጤክሰስ የቅራኔና የስምምነታቸው ታሪክ ነው። ይህ የሆነው የቤተ መቅደሱ ሥራ ካለቀ በኋላ ነው፤ ዕዝራ 4:24 ድረስ ተከታታይ የሆኑ የታሪክ ሁኔታዎች ናቸው።

# የእግዚአብሔር የማይለወጥ ቃል

## እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ይጠብቃል

መጽሐፈ ዕዝራ እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካኝነት ቃል ኪዳኑን እንዴት እንደፈጸመ ያሳየናል። ሕዝቡን እንደገና ወደ እስራኤል መለሰ፤ የአረመኔ ነገሥታትን ልብ አይሁዳውያንን እንዲረዱ አነሣሣ። መሪዎችና ነቢያት ሕዝቡን እንዲመሩና በመንፈስ እንዲያበረታቷቸው አስነሣ።

## እውነተኛ አምልኮ ተገኘ

አይሁዳውያን በየአገሩ ተበታትነው ሳለ አምልኮ አቁመው ነበር። ሆኖም እግዚአብሔር ቃል እንደገባው ወደ አገራቸው መለሳቸው። ቤተ መቅደሱን እንደገና በሙሴ ሕግ ላይ እንደተጻፈው ዓይነት አምልኮ እንዲያመልኩ ረዳቸው። አይሁዳውያን ወደ አገራቸው ተመልሰው እግዚአብሔርን ማምለክ ጀመሩ።

# የዕዝራ 3-6 ማጠቃለያ

እግዚአብሔር ለብዙ ዓመታት ታማኝነቱን ለአይሁዳውያን አሳይቷቸዋል። ወደ አገራቸው ለመመለስ ፈቃደኛ የነበሩ ሁሉ ቤታቸውን በየሠፈራቸውና በየከተሞቻቸው ሊሠሩ ይችሉ ነበር። በመሥዋዕትና የበዓልን ቀናት በማሰብ እንዲያመልኩ እግዚአብሔር መራቸው።

እስራኤላውያን ወደ ኢየሩሳሌም ከተመለሱ በኋላ ኑሮ ቀላል አልነበረም። በይሁዳ ያሉት ሹማምንት ይቃወሟቸው ነበር። የቤተ መቅደሱን ግንባታ እንዳይቀጥሉ ስላደረጓቸው በመጨረሻ ሥራውን እንዲያቆሙ ተገደዱ።

እግዚአብሔር የፋርስ አረመኔ ነገሥታትን ልብ ማነሣሣት ጀመረ። ቂሮስ ብዙ አይሁዳውያንን ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመልስ እግዚአብሔር አነሣሣው። እንደገና ቤተ መቅደሱ ተሠርቶ እንዲያልቅ ትዕዛዝ እንዲሰጥ እግዚአብሔር የዳርዮስን ልብ አነሣሣ።

ሐጌና ዘካርያስ ሕዝቡን እንዲያበረታቱና እንዲያስተምሩ እግዚአብሔር አስነሣቸው። እነርሱም የቤተ መቅደሱን ሥራ እንዲጨርሱ አይሁዳውያንን አበረታቷቸው። ካህናቱና ሌዋውያን ሕዝቡን በአንድ ላይ ሰብስበው የቤተ መቅደሱን ሥራ ጨረሱ።

## ጥያቄዎች ዕዝራ 3-6

1. እስራኤላውያን ወደ ይሁዳ ተመልሰው በየመንደሮቻቸውና በየከተሞቻቸው ከሠፈሩ በኋላ መጀመሪያ የደረጉት ምንድነው?
2. በቤተ መቅደሱ ግንባታ ወቅት የነበሩት ነቢያት እነማን ናቸው?
3. የቤተ መቅደሱ ግንባታ የተቋረጠው ለስንት ዓመታት ነው?
4. አይሁዳውያን ወደ አገራቸው እንዲመለሱና ቤተ መቅደሱን እንዲሠሩ የረዷቸው የፋርስ ነገሥታት እነማን ናቸው?
5. ባቢሎን ውስጥ ስለቀሩት እስራኤላውያን ያለን መረጃ ምንድነው?
6. እስራኤላውያን ቤተ መቅደሱን ለመገንባት ዕቃዎቹን ያገኙት ከየት ነው?
7. የቤተ መቅደሱን ግንባታ የተቃወሙት እነማን ነበሩ? ምን አደረጉ?
8. እግዚአብሔር የቤተ መቅደሱ ሥራ እንዲያልቅ ትዕዛዝ እንዲሰጥ እንደገና ያነሣሣው ንጉሥ ማን ነው?
9. ሥራው እንዲፈጸም ሕዝቡን ያነሣሣው ማን ነው?
10. የቤተ መቅደሱ ሥራ ካለቀ በኋላ እስራኤላውያን ያከበሩት በዓል ምን ነበር?



# ክፍል ሦስት የዕዝራ ወደ ኢየሩሳሌም መመለስ ዕዝራ 7-10

## ታሪካዊ አቀማመጥ

### በምዕራፍ 6 እና 7 መካከል ያለው ጊዜ

በዕዝራ 6 እና 7 መካከል ወደ 57 ዓመታት አሉ። ዳርዮስ ሌላ 30 ዓመት ሲገዛ ልጁ ጤክስስ ደግሞ 20 ዓመት ገዝቷል። ዕዝራ ሌላውን ቡድን የመራው በአርጤክስስ በሰባተኛው ዘመነ መንግሥት ነበር።

## የዕዝራ 7-10 መግቢያ አስተያየቶች

### ዕዝራ በባቢሎን ውስጥ

ዕዝራ ያደገው በባቢሎን ውስጥ ነበር። በንጉሡም ዘንድ የታወቀ ነበር። ሁለተኛውን ቡድን ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመራ እግዚአብሔር ልቡን ባነሣሣ ጊዜ ንጉሡ ደገፈው። ንጉሥ ቂሮስ በዘሩባቤል ጊዜ እቃጅ እንዳወጀው ሁሉ ንጉሥ አርጤክስስም ዕዝራ ሲመለስ አዋጁን አወጀ።

### ዕዝራ ካህንና ፀሐፊ

ዕዝራ ካህን ቢሆንም እንደ ጸሐፊ ያገለግል ነበር። በዚያን ጊዜ የጸሐፊ ሥራ ሕግጋቱን መጻፍ ነበር። ሆኖም ዋናው ነገር ሕጉን ማጥናትና ማስተማር ነበር። ዕዝራ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ለእስራኤላውያን ሕግጋቱን እንዲያስተምር በእግዚአብሔር ተመረጠ።

### የዕዝራ የአስተዳደር ሥልጣን

ንጉሡ ዕዝራ እንዲመራ፥ እንዲቀጣና ዕቃዎችን ለመግዛት የቀረጥ ገንዘብ እንዲሰበስብ ሥልጣን ሰጠው። በቤተ መቅደሱ ሥራ ላይ ተካፋይ የነበሩት ቀረጥ ከመክፈል ነፃ ነበሩ። ንጉሥ አርጤክስስ ዕዝራን ያምነው ነበር። ነገር ግን ዕዝራ ክብሩን ሁሉ ለእግዚአብሔር ሰጠ። ይህ ሊሆን የቻለው እግዚአብሔር በንጉሡ ልብ ውስጥ እምነት እንዲኖር ስላደረገ ነው ብሎ ዕዝራ አመነ።

# የዕዝራ ታሪክ 7-10

## ዕዝራ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ

ሌላውን የእስራኤላውያንን ቡድን እንዲመራ እግዚአብሔር የዕዝራን ልብ አነሣሣ። ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱት እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ሕግ መማር እንደሚያስፈልጋቸው ዕዝራ ቀድሞ ሰምቷል። ሀሳቡን ለንጉሥ አርጤክስስ ሲያቀርብ ንጉሡም በሀሳቡ ተስማማ። ወደ አገራቸው ለመመለስ ፈቃደኛ የሆኑ ሁሉ መመለስ እንደሚችሉ አዋጅ ተነገረ።

## የአርጤክስስ አዋጅ

ወደ ኢየሩሳሌም መመለስ የሚፈልጉ እስራኤላውያን ሁሉ መመለስ እንደሚችሉ አርጤክስስ አወጀ። ንጉሡና የንጉሡ አማካሪዎች ለመሥዋዕት የሚቀርቡ እንስሳት መግዣ እንዲሆኑ ወርቅና ብር ሰጡ። ዕዝራ ለቤተ መቅደሱ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ዕቃዎችን ከንጉሡ ማግኘት ይችል ነበር። በምዕራብ ኤፍራጥስ ያሉት የቅርሱ ባለሥልጣናት ለቤተ መቅደሱ አስፈላጊ የሆነውን ሁሉ እንዲሰጡና ከካህናቱ፥ ከሌዋውያን፥ ከዘማሪዎች፥ ከጠባቂዎችና ከቤተ መቅደሱ ሠራተኞች የቀረጥ ገንዘብ እንዳይሰበስቡ አርጤክስስ አዘዘ።

## ዕዝራ እግዚአብሔርን አመሰገነ

ዕዝራ ጸሎቱ ስለተሰማ እግዚአብሔርን አመሰገነ። በኢየሩሳሌም ያለውን የእግዚአብሔርን ቤት ለማክበር ፈቃደኛ ስለነበረ ንጉሡንም አመሰገነ። በእግዚአብሔር መልካም ፈቃድ ከንጉሡ አማካሪዎች እርዳታ ስላገኘ ዕዝራ ተደሰተ። ብዙ እስራኤላውያን መሪዎችም ከእርሱ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ እሺ እንዲያሰኛቸው እግዚአብሔር ስላበረታታው ዕዝራ ምስጋና አቀረበ።

## ሕዝቡ ወደ ኢየሩሳሌም ለመመለስ ተዘጋጀ

ዕዝራ የእስራኤላውያንን መሪዎች ሁሉ መዘገበ። ከእርሱ ጋር የሚሄዱትን ሁሉ ሲመዘግብ ካህናት እንጂ ሌዋውያን እንደሌሉ አየ። ለሌዋውያንና ለቤተ መቅደሱ ሠራተኞች መልዕክት ልኮ እርሱ ከሚመራው ቡድን ጋር እንዲደባለቁ ጠየቃቸው። ሁሉንም በስማቸው ከመዘገበ በኋላ ቀሪውን ጊዜ እግዚአብሔር በጉዞአቸው እንዲረዳቸው በጾምና በጸሎት አሳለፉ። ዕዝራ ወርቁንና ብሩን መዝኖ ኢየሩሳሌም ውስጥ ወዳለው ቤተ መቅደስ እንዲወስዱ ለመሪዎቹ ካህናት ሰጣቸው፤ 8፡1-30።

## ምርኮኞች ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ

ሰዎች ከፋርስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለሱ እግዚአብሔር ጸሎታቸውን ሰምቶ ከሚያጠቋቸው ጠላቶች ሁሉ ተከላከላቸው። የተነሡት ሁሉ በሰላም ከኢየሩሳሌም ደረሱ። ሦስት ቀን ካረፉ በኋላ ካህናት ወደ ቤተ መቅደስ ሄደው የተረከቡትን ብርና ወርቅ ሁሉ



አስመዝነው ለቤተ መቅደስ ጠባቂዎች አስረከቡ። የተመለሱት ሰዎች ሁሉ ለቤተ መቅደስ ሥጦታቸውን ሰጡ። ለአምላካቸው የሚቃጠለውን መሥዋዕት ለማቅረብ እንስሶችን አቀረቡ። አርጤክስስ የሰጣቸውን ፈቃድ ይዘው ወደ ባለሥልጣኖች ዘንድ ሄደው ሰጡት። ምርኮኞቹ የቤተ መቅደስ አምልኮ ለመቀጠል ሲፈልጉ ከእነዚህ ባለሥልጣኖች ድጋፍ አገኙ፤ ዕዝራ 8፡31-36።

## ዕዝራ የሕዝቡን ኃጢአት ተናዘዘ

ዕዝራና ሕዝቡ በኢየሩሳሌም ከሠፈሩ በኋላ አንዳንድ መሪዎች ከዕዝራ ጋር ሊነጋገሩ መጡ። ካህናቱ፥ ሕዝቡና ሌዋውያን ከጐረቤቶቻቸው ጋር እንደተጋቡ ነገሩት። ዕዝራ ይህንን ሲሰማ ልብሱን በንዴት ቀደደ፤ ፀጉሩንም ነጨ። በማታው መሥዋዕት ጊዜ ዕዝራ የሕዝቡን ኃጢአት ለመናዘዝ ለእግዚአብሔር ጸለየ። በፋርስ ውስጥ የነበራቸውን የምርኮ ዘመን ስላስታወሳቸውና በሰላም ወደ አገራቸው ስለመለሳቸው እግዚአብሔርን አመሰገነ። ዕዝራ ስለ ሕዝቡ ኃጢአት ሲናዘዝ ብዙ እስራኤላውያን፥ ወንዶች፥ ሴቶችና ልጆች ተሰብስበው አለቀሱ።

## ኃጢአት በሠሩት ላይ የተፈረደው ፍርድ

ከውጭ ሚስት ያገቡ ሁሉ በኢየሩሳሌም ተሰበሰቡ። ዕዝራ ሲያነጋግራቸው ዝናብ ውስጥ ቆመው ነበር። ጥፋታቸውን አምነው ከሚስቶቻቸው ለመለየት ተስማሙ። ዕዝራ ከውጭ ሚስት ያገቡት ሁሉ እንዲመዘገቡ መሪዎች አዘጋጀ። ሁሉም ሚስቶቻቸውን ለመፍታት ተስማምተው ስለ ኃጢአታቸው መሥዋዕት አቀረቡ።

# ጥያቄዎች ዕዝራ 7-10

1. ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሰው ቡድን ውስጥ ስንት ሰዎች ነበሩ?

መልስ፦ በጠቅላላ የተመዘገቡት 1514 ነበሩ። ሆኖም እነዚህ ትልልቆቹ ሰዎች ብቻ ናቸው። ሴቶቹና ሕፃናቱ 6000 ይሆናሉ።

2. በአካባቢው ካሉት አገሮች ጋር ስለመለያየት እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰጠው ትዕዛዝ ምንድነው?

መልስ፦ ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብፅ ወደ ተስፋው ምድር ወደ ከነዓን ሲመራ እግዚአብሔር ጥብቅ ትዕዛዝ ሰጥቶ ነበር። እስራኤላውያንን ከእግዚአብሔር ዘንድ ሊያርቋቸው ስለሚችሉ ከሌሎች ጐሣዎች ጋር መጋባት አይፈቀድላቸውም ነበር፤ ዘዳግም 7፡1-6።

3. ዕዝራ 7፡9 ላይ ዕዝራ የሚመራው ቡድን በመጀመሪያው ወር በመጀመሪያው ቀን መነሣቱን ይናገራል። ዕዝራ 8፡31 ላይ በመጀመሪያው ወር በአሥራ ሁለተኛው ቀን መነሣታቸውን ይናገራል። ይህ ልዩነት እንዴት ተፈጠረ?

መልስ፦ መጀመሪያ ዕዝራ ከእርሱ ጋር የሚሄዱት በአኀዋ ውስጥ እንዲሰበሰቡ ጠራቸው። በአኀዋ ውስጥ ለመሰብሰብ ዘጠኝ ቀን ወሰደባቸው። በአሥራ ሁለተኛው ቀን ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ጉዞ ከመጀመራቸው በፊት በአኀዋ ውስጥ ለሦስት ቀናት ቆዩ።

# የእግዚአብሔር የማይለወጥ ቃል

## እግዚአብሔር በምርኮ የነበሩትን የእስራኤላውያንን ልብ አነሣሣ

እስራኤላውያን በየአገሩ ለመበታተናቸው ዋናው ምክንያት ኃጢአትና ለእግዚአብሔር አለመታዘዛቸው ነበር። በባቢሎንና በሌሎች የፋርስ ግዛቶች ውስጥ ሠፍረው ነበር። ብዙዎች በሌሎች አገር ውስጥ እንዲቆዩ ተይዘው ነበር። ቢሆንም ወደ አገራቸው መመለስ ስሚፈልጉ እስራኤላውያን መሪዎች እንዲሆኑ እግዚአብሔር ሰዎችን አስነሣ። መጀመሪያ ዘሩባቤልን ቀጥሎም ዕዝራን አስነሣ። በእነርሱ መሪነት ብዙዎች ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ እግዚአብሔር አነሣሣቸው።

## የተመለሱትን እግዚአብሔር ጠበቃቸው

ከባቢሎን እስከ ኢየሩሳሌም ድረስ ረጅምና አደገኛ መንገድ ነው። አራት ወር ይፈጃል! ዕዝራ 7:9። ከባቢሎን ከመነሣታቸው በፊት ዕዝራ ከሕዝቡ ጋር ጸለየ! ዕዝራ 8:23። እግዚአብሔር ጸሎቱን ሰምቶ ካለወታደር ጥበቃ በደህና እንዲደርሱ ረዳቸው።

## እግዚአብሔር ለሕዝቡ ይቅርታ አደረገ

ወደ ኢየሩሳሌም ከዘሩባቤል ጋራ የተመለሰው የመጀመሪያው ቡድን ለእግዚአብሔር ታማኝ አልነበረም። ጐረቤቶቻቸው ከሆኑት ከአረመኔ ሴቶች ጋር ተጋቡ። በዚሁ ምክንያት ዕዝራ በጣም አዝና ኃጢአታቸውን ይቅር እንዲላቸው ወደ እግዚአብሔር ጮኸ። ሕዝቡም ንስሐ ገብተው ከእግዚአብሔር መንገድ ያራቋቸውን አረመኔ ሚስቶቻቸውን ፈቱ። ይህ በምርኮ እንዲያዙ ካደረጓቸው ኃጢአቶች አንዱ ነው። እግዚአብሔር ንስሐቸውን ሰማቸው።

# ማጠቃለያ ዕዝራ 7-10

ዘሩባቤል የመጀመሪያዎቹን እስራኤላውያን ወደ አገራቸው ከመራ ከ50 ዓመት በላይ ሆነ። በኢየሩሳሌም ያለው ቤተ መቅደስ ተሠርቷል! ነገር ግን ሰዎቹ ከአረመኔ ጐረቤቶቻቸው አልተለዩም። በባቢሎን ውስጥ ካህንና ጸሐፊ የነበረው ዕዝራ ይሁዳ ውስጥ ስለነበሩ ሰዎች ሰማ። ሌሎች እስራኤላውያንን ወደ ኢየሩሳሌም ለመመለስ ንጉሥ አርጤክስስን ፈቃድ እንዲጠይቅ እግዚአብሔር ዕዝራን መራው።

ከ1500 የሚበልጡ ሰዎች ከሚስቶቻቸውና ከልጆቻቸው ጋር በዕዝራ እየተመሩ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱ። እግዚአብሔር በረጅሙና በአደገኛው መንገዳቸው ሁሉ ጠበቃቸው።

ኢየሩሳሌም እንደደረሱ ካህናቱ፣ ሌዋውያንና ሕዝቡ ከጐረቤቶቻቸው ጋር እንደተጋቡ አየ። ሕዝቡን ይቅር እንዲል ወደ እግዚአብሔር ጮኸ። ሰዎቹ ዕዝራን ሲያዩ ንስሐ እየገቡ ሚስቶቻቸውን እንደሚፈቱ ተናገሩ። እያንዳንዳቸው እየተመረመሩ ፍርድ ተፈረደባቸው። ሚስቶቻቸውን ፈትተው ስለኃጢአታቸው ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቀረቡ።



# ጥያቄዎች ዕዝራ 7-10

1. ከዕዝራ 6-7 ስንት ዓመታት አሉ?
2. ከዕዝራ 6-7 ባሉት ዓመታት ውስጥ የፋርስ ነገሥታት እነማን ነበሩ?
3. ዕዝራ ማን ነው? ሥራውስ ምን ነበር?
4. ዕዝራ ንጉሥ አርጤክስስን ፈቃድ የጠየቀው ስለምንድነው?
5. ንጉሥ አርጤክስስ ስዕዝራ ያደረገው ዝግጅት ምን ነበር? ምን ሥልጣን ነበረው?
6. ዕዝራ እግዚአብሔርን ለምን ለምን ነገሮች አመሰገነ?
7. ዕዝራ ኢየሩሳሌም ሲደርስ እዚያ በነበሩት እስራኤላውያን ላይ ያየው ችግር ምንድነው?
8. እግዚአብሔር ጋብቻን በሚመለከት የሰጠው ሕግ ምንድነው?
9. ዕዝራና እርሱ የሚመራቸው ሰዎች ኢየሩሳሌም ለመድረስ ምን ያህል ጊዜ ወሰደባቸው?
10. ዕዝራና እስራኤላውያን ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለሱ እግዚአብሔር ታማኝነቱን እንዴት አሳያቸው? ስለእግዚአብሔር ታማኝነት ሦስት ማስረጃዎችን ጻፍ።

# ክፍል አራት ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ

## ነህምያ 1-2

| ሁኔታ | ወቅቱ | የፋርስ ንጉሥ | የተጠቀሱ መጻሕፍት |
|---|---|---|---|
| ነህምያ ሦስተኛውን የእስራኤላውያንን ቡድን ወደ ኢየሩሳሌም መራ። | 445 ከክርስቶስ ልደት በፊት | አርጤክስስ 1 | ነህምያ 2 |

### የነህምያ ቤተሰብ

የነህምያ አባት ሐካልያ ነው። ነህምያ አናኒ የሚባል ወንድም ነበረው፤ ነህምያ 1፡2 እና 7፡2 ከአሥራ ሁለቱ ነገዶች ከየትኛው እንደመጣ የተገኘ መረጃ የለም። ነህምያ የተወለደው በምርኮው ጊዜ በባቢሎን ውስጥ ነው።

### የነህምያ ሥራ

ነህምያ የንጉሥ አርጤክስስ ጽዋ አሳላፊ ነበረ። ንጉሡ ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለስና የይሁዳ አስተዳዳሪ እንዲሆን ፈቀደለት። ነህምያ ለአሥራ ሁለት ዓመት ገዢ ሆነ፤ ነህምያ 5፡14፤ 8፡9 እና 10፡1።

### በመጽሐፈ ነህምያ ውስጥ የተሸፈነው ጊዜ

የነህምያ ታሪክ መመዝገብ የተጀመረው የዕዝራ መጽሐፍ ካለቀ ከአሥራ ሁለት ዓመት በኋላ ነበር። መጽሐፈ ነህምያ ሌላ አሥራ ሁለት ዓመት ይሸፍናል። ነህምያ ምዕራፍ 1-12 ውስጥ የተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ነህምያ እስራኤላውያንን ሲመራ በነበረባቸው በመጀመሪያው ዓመት የተፈጠሩ ናቸው። ይህም በንጉሥ አርጤክስስ በሃያኛው የአገዛዝ ዓመት ነበር።



### እስራኤላውያን በኢየሩሳሌም ውስጥ የነበራቸው ሁኔታ

በዕዝራ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ ከተጠቀሰው መንፈሳዊ እንቅስቃሴ አሥራ ሁለት ወይም አሥራ ሦስት ዓመታት አልፈዋል። ቢሆንም ሕዝቡ በመንፈስ ጠንካራ አልነበረም። በዚያን ጊዜ አስፈላጊ መከላከያ የነበሩትን የፈራረሱትን ግድግዳዎችም መገንባት አልቻሉም ነበር።

### ነህምያ የተመለሰው በጸሎት ተደግፎ ነው

በኢየሩሳሌም የነበረውን ችግር ሲሰማ ነህምያ ለሦስት ወራት እያለቀሰ ጸለየ። የእስራኤልን ኃጢአት ተናዞ እግዚብሔር ምሕረት እንዲአደርግላቸው ለመነ። ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሄድ ንጉሡ እንዲፈቅድለት እግዚአብሔር ልቡን እንዲያነሣሣ ጸለየ።

## የነህምያ ታሪክ

### ነህምያ ኢየሩሳሌም ውስጥ የነበረውን ችግር አየ

ነህምያ አሳላፊ ሆኖ ለፋርሱ ንጉሥ ያገለግል ነበር። ይህ ሥራ በመንግሥቱ ውስጥ ከባድ ኃላፊነትን የሚጠይቅ ነበር። ማንም ሰው ንጉሡን እንዳይበክለው ከመብላቱና ከመጠጣቱ በፊት ነህምያ መቅመስ ነበረበት።

ከነህምያ ወንድም ከአናኒ ጭምር አንዳንድ እስራኤላውያን ከኢየሩሳሌም መልዕክት ይዘው መጡ። መልዕክቱም የሚያሳዝን ነበር። ነህምያ ይሁዳ ውስጥ ችግር እንዳለ አየ። እስራኤላውያን ፈርተውና ተጨንቀው እንዲሁም የኢየሩሳሌም አጥሮችና በሮች ፈራርሰው ነበር። ይህ ዜና ነህምያን በጣም ስላሳዘነው ለኢየሩሳሌም መጾምና መጸለይ ጀመረ፤ ነህምያ 1፡1-4ን አንብብ።

### የነህምያ ጸሎት

እግዚአብሔር ታማኝ ስለሆነና ለታዘዙት ቃሉን ስለጠበቀ ነህምያ አመሰገነ። ለእግዚአብሔር ለታላቁ አምላክ ጸለየ። ጸሎቱም እንዲሰማ ለመነ። እርሱም አባቱም ኃጢአት እንደሠሩ ተናዘዘ። «በሙሴ በኩል የሰጠኸውን ትዕዛዝ አልጠበቅንም፤ ታማኞች ስላልነበርን በየአገሩ ተበታተንን። ይህ ሕዝብ እንደገና የመለስከው ሕዝብ ነው» አለ። ነህምያ ሕዝቡ እንደገና እንዲመለስ ስለረዳው እግዚአብሔርን አመሰገነ። ንጉሡ ውለታ እንዲሠራለት እንዲያደርግ እግዚአብሔርን ለመነ፤ ነህምያ 1፡5-11 አንብብ።

### ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሄድ ንጉሥ አርጤክስስ ፈቀደለት

አንድ ቀን ነህምያ ንጉሡንና ንግሥቷን እያስተናገደ ሳለ ንጉሡ ለምን እንዳዘነ ነህምያን ጠየቀው። ነህምያ ቢደነቅም «የአባቴ አገርና አጥሮችዋ ሲፈራርሱ እንዴት ልደሰት?» ብሎ መለሰለት። ንጉሡ ምን እንደሚፈልግ በጠየቀው ጊዜ ነህምያ በልቡ እግዚአብሔርን

ጸለየ። እግዚአብሔር የነህምያን ጸሎት መለሰ። ንጉሡ እንዲሄድ ፈቅዶ ከርሱም ጋር የሠራዊት አለቆችና ለግንባታው ሥራ የሚያገለግል እንጨት እንዲቆርጥ የሚረዳ ፈቃድ ላከለት።

አንድ ማታ በኢየሩሳሌም ውስጥ ተደብቆ ወጥቶ የፈራረሱትን ቅጥሮች አጠና። ካህናቱንና መሪዎቹን ሰብስቦ የበሮቹ መፈራረስ ለእግዚአብሔር ስም ውርደት መሆኑን በነገራቸው ጊዜ ሁሉም ለመገንባት ተስማሙ።

በኢየሩሳሌም ያሉት የእስራኤላውያን ጠላቶች የግንባታውን ሥራ ተቃወሙ። እያፌዙባቸው ለንጉሡ የማይታዘዙ ናቸው አሉ። ነገር ግን ይህ ሥራውን አላቆመውም፤ እስራኤላውያንና ነህምያ በሐሳባቸው ጸኑ።

## ጥያቄዎች ነህምያ 1-2

1. ነህምያ በኢየሩሳሌም ያሉት በሮችና ቅጥሮች መፈራረሳቸውን የሰማው ከማን ነው?
2. በፋርስ ርዕሰ ከተማ በሱሳ ውስጥ የነህምያ ሥራ ምን ነበረ?
3. በነህምያ ጊዜ የነበረው የፋርስ ንጉሥ ማን ነው?
4. ከዕዝራ መጽሐፍ መጨረሻ እስከ መጽሐፈ ነህምያ መጀመሪያ ድረስ ስንት ዓመታት አለፉ?
5. ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ውስጥ የነበሩት የእስራኤላውያን መንፈሳዊ ሁኔታ እንዴት ነበር?
6. ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ሲጸልይ እግዚአብሔር ጸሎቱን የመለሰለት እንዴት ነው? አራት ነገሮችን ጻፍ።
7. ነህምያ ቅጥሮቹን ያየው መቼ ነው?
8. በቅጥሮቹ ግንባታ ላይ ለመርዳት የተስማሙት እነማን ናቸው?
9. የግንባታውን ሥራ ለማቆም የሞከሩት ጠላቶች እነማን ናቸው? ስማቸውንና ምን እንደነበሩ ጻፍ /ጻፊ/።
10. ነህምያ 2፡17ን አንብበህ /አንብበሽ/ ነህምያ የግንባታውን ሥራ ለመሥራት የሰጠውን ምክንያት እይ /እዩ/።



# ክፍል አምስት የኢየሩሳሌም በሮች ተገነቡ

## ነህምያ 3-7 ታሪካዊ አቀማመጥ

ቴቁሐውያን፡- እነዚህ ከደቡብ ኢየሩሳሌም አሥራ ስድስት ኪሎ ሜትር ርቃ ከምትገኝ ከቴቁሐ የመጡ ናቸው። ቴቁሐ ከዓረባዊው ጌሳም አገር ጋር ትዋሰናለች፤ ነህምያ 3፡5።

አሽዶዳውያን፡- አሽዶድ በምዕራብ ኢየሩሳሌም የምትገኝ የቀድሞ የፍልስጥኤም ከተማ ናት። በነህምያ ጊዜ አሽዶድ የፋርስ መንግሥት መሰብሰቢያ ነበረች። ሹማምንቱም ነህምያን ተቃወሙት፤ ነህምያ 4፡7። ሆኖም ነህምያ ቅጥሮቹን ለመገንባት የሚያስችለውን ደብዳቤ ከንጉሡ አግኝቶ ነበር።




## መኅበራዊ ችግሮች

1. መሬት የሌላቸው የሚያገኙት ምግብ ጥቂት ነበር።
2. መሬት የነበራቸው በድርቁ ምክንያት መሬታቸውን እያስያዙ ገንዘብ ይበደሩ ነበር።
3. ሌሎች ለፋርሱ መንግሥት የመሬት ግብር ለመክፈል ገንዘብ መበደር አለባቸው።
4. ከፍ ያለ ማዕረግ ያላቸው እስራኤላውያን ብድራቸውን መክፈል ያልቻሉትን ለውጭ ጌታዎች እንደባሪያ ይሸጧቸዋል።

# ነህምያ 3-7 ታሪኩ ባጭሩ

ከሃያኛው እስከ ሰላሳ ሁለተኛው የአርጤክስስ ዘመነ መንግሥት ድረስ ነህምያ ኢየሩሳሌም ውስጥ ነበረ፤ ነህምያ 2፡1 እና 13፡6። ከዚያም ነህምያ ወደ ባቢሎን ተመለሰ። ቆይቶም ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ፤ ነህምያ 13፡6። በሁለተኛው ጊዜ ለምን ያህል ጊዜ ኢየሩሳሌም ውስጥ እንደቆየ የሚናገር መዝገብ የለም።

ነህምያ የከተማውን ግንቦች እንዲገነባ ከንጉሡ ሥልጣን ተሰጠው። ኢየሩሳሌምንም እንዲገዛ ሥልጣን ሰጠው። እስራኤላውያን ብዙ የሚታረሙ ትክክል ያልሆኑ ነገሮችን ይሠሩ ስለነበር ነህምያ ይህንን ሁሉ ማስተካከል ነበረበት።

# የነህምያ ታሪክ

## የኢየሩሳሌም ግንቦች እንደገና ተገነቡ

እያንዳንዱ ሰው ቅርቡ ያለውን የፈረሰ አጥር መገንባት እንዳለበት ነህምያ አቀደ። ሕዝቡንና ቤቱን መከላከል ስለሚፈልግ አጥሩን ለመሥራት ፈቃደኛ ነበር። አንዳንዶቹ ሁለት ሁለት ክፍል ሠሩ፤ ነህምያ 3፡27-28።

ማዕረግ ያላቸው ሰዎች ሁሉ በግንባታው ሥራ ላይ ተካፈሉ። ካህናት፣ ወርቅ አንጣሪዎች፣ ሌዋውያንም፣ ሴቶችና ነጋዴዎች ሥራው ላይ ነበሩ፤ ነህምያ 3።

## ጠላቶች የግንባታውን ሥራ ተቃወሙ

የነህምያ ጠላቶች በተለያዩ መንገዶች ሥራውን ለማደናቀፍ ወይም ለማቆም ሞከሩ። የሰማርያው ገዢ ሰንባላጥ ነህምያና እስራኤላውያኑ ላይ አላገጠባቸው። ሆኖም ነህምያ ጸለየ፤ እስራኤላውያንም ለመሥራት ሀሳብ ነበራቸው። ሰንባላጥ፣ ጦብያ፣ ጌሳምና የአሽዶድና የአሞን ሰዎች የአጥሮቹ ሥራ እየቀጠለ መሆኑን ሲያዩ በጣም ተናደዱ። ኢየሩሳሌምን ለማጥቃት ተነሡ። እስራኤላውያን እንደገና ጸልየው አጥሩን ሌትና ቀን መጠበቅ ጀመሩ። የሚሠሩትም ሰይፍ ይዘው ነበር። ግማሾቹ ሲሠሩ ሌሎቹ ለጥበቃ ይቆማሉ። የእምቢልታውን ድምፅ ከሰሙ ለመዋጋት ዝግጁ ነበሩ። የአጥሮቹን ሥራ የሚደግፉና የሚረዱ ከኢየሩሳሌም ውጭ ያሉ ሰዎች ማታ ማታ ኢየሩሳሌም ውስጥ ይቆዩ ነበር። ነህምያና ጠባቂዎቹ ከተማቸውን ከጥቃት ለመጠበቅ ልብሳቸውን ላያወልቁ ይተኙ ነበር፤ ምዕ.4ን አንብቡ።

## ድሃዎቹ ይጭቆኑ ነበር

ብዙዎቹ እስራኤላውያን ብዙ የሚያስፈልጓቸው ነገሮች ነበሩ። አንዳንዶች ቤተሰባቸውን የሚያበሉት ምግብ የላቸውም። አንዳንዶች ገንዘብ ለማግኘት መሬታቸውን፣ የወይን እርሻቸውንና ቤታቸውን ማስያዝ ነበረባቸው። ሌሎች ለመሬታቸውና ለሰብላቸው ግብር ለመክፈል ገንዘብ መበደር ነበረባቸው። አንዳንዶች ዕዳቸውን ለመክፈል ልጆቻቸውን እንደ ባሪያ መሸጥ ነበረባቸው።

ነህምያ ስለዚሁ ነገር የእስራኤላውያንን መሪዎች ዘለፋቸው። ሕዝቡን እየጭቆኑና ወንድሞቻቸውን ለባርነት እንዲሸጡ እያስገደዷቸው መሆኑን ነገራቸው። «ትክክል ያልሆነ ሥራ እየሠራችሁ ነው። እግዚአብሔርን በመፍራት ትክክል የሆነውን ብትሠሩ ጠላቶቻችን አያሾፉብንም። ያበደርነው ገንዘብ እንዲከፈለን አንጠይቅ። ዕዳዎቻቸውን ሁሉ ሽሩላቸው፤ የወይን እርሻዎቻቸውን፣ መሬታቸውንና ቤታቸውን መልሱላቸው» ብሎ ነህምያ ለእስራኤላውያን መሪዎች ትዕዛዝ ሰጠ። መሪዎቹ በሀሳቡ ተስማሙ። ቃላቸውን እንዲጠብቁ ነህምያ አስማላቸው። ሁሉም ስለስምምነቱ እግዚአብሔርን አመሰገኑ፤ ነህምያ 5፡1-13።

## ነህምያ የለጋስ ሰው ምሳሌ ነበር

ነህምያ ለአሥራ ሁለት ዓመታት የይሁዳ ገዢ ነበር። በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ማንኛውም ገዢ ማድረግ እንደሚገባው የግብር ገንዘብ አልጠየቀም። በየቀኑ 150 እስራኤላውያንንና አለቆቻቸውን እንዲሁም ከሌላ ቦታ ሊጎበኙት የሚመጡትን ሁሉ ይመግብ ነበር። ነህምያና የነህምያ ሠራተኞች በግንባታው ሥራ ተካፋይ ነበሩ፤ ነህምያ 5፡14-19።

## ጠላቶች እስራኤላውያንን ለማጥቃት ተነሡ

የአጥሮቹ ሥራ በፍጥነት ስለቀጠለ ጠላቶቻቸው ተናደዱ። የግንባታው ሥራ እያለቀ ስለሆነ ለጦርነት አስቸጋሪ ስለነበረ የእስራኤላውያን ጠላቶች ነህምያን ከከተማው ለማስወጣት ሞከሩ። 62 ኪሎ ሜትር ከኢየሩሳሌም ርቃ በምትገኝ ኦኖ በምትባል ሜዳ እንዲገናኛቸው ለነህምያ መልዕክት ላኩ። አምስት ጊዜ መልዕክት ላኩበት። እስራኤላውያን መንግሥት ሊገለብጡ ነው ብለው ከሰሷቸው። ቢሆንም ነህምያ «አስፈላጊ የሆነ ሥራ እየሠራሁ ስለሆነ ወደ እናንተ ልመጣ አልችልም» ብሎ መልዕክት ላከባቸው። ጠላቶቹን መቋቋም እንዲያስችለው ወደ እግዚአብሔር ጸለየ።

ነቢዩ ሸማያ አንድ ሰው ነህምያን ሊገድል እንዳሰበ ለነህምያ ነገረው። በፍጥነት መጥቶ ቤተ መቅደሱ ውስጥ እንዲሸሸግ ጠየቀው። ነህምያ በጸለየ ጊዜ ስሙን ሊያጠፉ ካህናት ብቻ የሚገቡበትን ቤተ መቅደስ ውስጥ እንዲገባ ለማድረግ ሰንባላጥና ጦብያ ነቢዩን መክፈላቸውን ነህምያ ተገነዘበ» ነህምያ አልታለለም፤ የግንባታውም ሥራ ቀጠለ፤ ነህምያ 6፡1-4።

## ግንቦቹ ተሠርተው አለቁ

ጠላቶች ሥራውን ለማስቆም ቢሞክሩም የግንቦቹ ግንባታ ቀጠለ። እንደተመለከትነው የጎረቤት አገር ገዢዎች ሥራውን ለማስቆም ሞክረው ነበር። ነህምያ የሚናገረውን ሁሉ ለጦብያ ያስተላለፉ እስራኤላውያንም ነበሩ። ከዚያም ጦቢያ የማስፈራሪያ ደብዳቤ ለነህምያ ላከበት። ቢሆንም ሥራው በሃምሳ ሁለት ቀናት ውስጥ አለቀ። የከተማው መግቢያዎች ከተሠሩ በኋላ እንኳን ነህምያ በከተማው ዙሪያ ጠባቂዎች ያደርግ ነበር፤ ነህምያ 6፡15-19።

# ጥያቄዎች ነህምያ 3-7

1. ሳይዋጓቸው ጠላቶቻቸው ለምን ያስፈራሯቸው ነበረ?

መልስ፦ ንጉሥ አርጤክስስ ግንቦቹን እንዲሠራ ለነህምያ ሥልጣን ሰጥቶ ስለነበረ በቀጥታ ውጊያ ለመጀመር ፈሩ። በምትኩ ሥራውን በማሾፍ ለማስቆም ወይም የነህምያን ስም በማጥፋት ወይም በሥልጣን ሥራውን ለማስቆም ሞከሩ።

2. በእስራኤላውያን መካከል ለነበሩት ማኅበራዊና ኤኮኖምያዊ ችግሮች ምክንያት ምንድነው?

መልስ፦ ብዙዎቹ ችግሮቻቸው ከእነርሱ ዘንድ የመጡ ነበሩ። የድሆችን ንብረትና ሰብል እየወሰዱ ልጆቻቸውን ባሪያ ያደርጉባቸው ነበር። እግዚአብሔር ለሰጣቸው ትዕዛዝ ታዛዦች አልነበሩም። ከስድስት ዓመት በኋላ መሬት መያዣና ብድራቸውን መመለስ ያልቻሉትን በነፃ ያሠሩ ነበር፤ ዘፀአት 22፡25 እና 21፡2።

# የእግዚአብሔር የማይለወጥ ቃል

## እግዚአብሔር ማስተዋልን ሰጠ

ጠላቶቻቸው በተለያዩ መንገዶች ነህምያን አታለው ሥራውን ለማስቆም ሞከሩ። እግዚአብሔር የጠላቶቻቸውን ማታለልና ማስፈራራት እስንዲያውቅ ለነህምያ ማስተዋልን ሰጠው። ነህምያ ሥራውን ለማቆም እሻፈረኝ ብሎ እግዚአብሔር በሰጠው ጥበብና ብርታት መሥራት ቀጠለ፤ ነህምያ 6፡12።

## ለእግዚአብሔር ሕግጋት አለመታዘዝ አለመባረክን ያመጣል

እስራኤላውያን ሕግጋቱን ባይጠብቁ ችግር እንደሚመጣባቸው እግዚአብሔር አስጠንቅቋቸው ነበር። በይሁዳ የነበሩት አብዛኞዎቹ ችግሮች በአለመታዘዝ ምክንያት የመጡ ነበሩ። ድርቅና ለመንግሥት ግብር መክፈል ሕዝቡን አደህይቶት ነበር። እርዳታ የሚፈልጉትን በመርዳት ፈንታ ታላላቅ እስራኤላውያን ከደሆቹ መሬትና ሰብል ይገዙ ነበር። ይህ የግብር ገንዘብ ያስገኛል፤ ግን ታላላቅ እስራኤላውያን ብድር ያለባቸውን ሰዎች መሬት እንደማስያዣ ይወስዱባቸው ነበር። ልጆቻቸውን እንደ ባሪያ ይጠቀሙባቸው ነበር። ነህምያ እስራኤላውያንን የማይለወጠውን የእግዚአብሔርን ሕግ አስታወሳቸው፤ እነዚህ ነገሮች ከተስተካከሉ በኋላ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ባረከ።

# የነህምያ 3-7 ማጠቃለያ

ነህምያ የፈራረሱትን የኢየሩሳሌም ግንቦች ለመገንባት ዋና ዓላማ ነበረው። በአቅራቢያቸው ያለውን የግንብ ክፍል እንዲገነቡ ሕዝቡን ጠየቀ። ቤታቸውን ከጠላት አደጋ



መጠበቅ ስለሚፈልጉ ቅጥሩን ለመሥራት ፈቃደኞች ነበሩ። ወንድና ሴት፥ ድሀና ሀብታም የከተማዋን ቅጥር ለመሥራት ተሰበሰቡ።

የእስራኤላውያን ጣላቶች የከተማው ግንቦች እንዲሠሩና እስራኤላውያን ጠንካሮች ሆነው ማየት አልፈለጉም። ነህምያ ግንቦቹን ለመሥራት ንጉሥ አርጤክስስ ሥልጣን ስለሰጠው ሥራውን ለማስቆም አልቻሉም። በማሾፍ፥ በማስፈራራት፥ በማታለል፥ በሐሰት ክስና የነህምያን ስም በማጥፋት ሥራውን ለማስቆም ሞከሩ። ቢሆንም ሥራው በሃምሳ ሁለት ቀናት ውስጥ አለቀ።

የምግብ ዋጋና የግብር ገንዘብ ከፍ በማለቱ ብዙ እስራኤላውያን እንዲደኸዩ አደረጋቸው። የእስራኤላውያን ታላላቅ ሰዎች ለራሳቸው ትርፍ ማግኛ ይህንን ችግር ተጠቀሙበት። መሬትና ሰብል ገዙ፤ ባለዕዳዎችን እንደ ባሪያ ማሠራት ጀመሩ። ይህ ከእግዚአብሔር ሕግ ውጭ ስለነበረ በሕዝቡ ላይ ትልቅ ችግር አስከተለ። ነህምያ መሬቶቹን እንዲመልሱ፥ ባሪያዎቹን ነፃ እንዲያደርጉና ለባለዕዳዎች ይቅርታ እንዲያደርጉ ታላላቅ እስራኤላውያንን ለመነ፤ እነርሱም በሀሳቡ ተስማሙ።

ነህምያ ለሕዝቡ ምሳሌ ነበር። አስተዳዳሪ ቢሆንም ከሕዝቡ ገንዘብ አልጠየቀም። በምትኩ ብዙ እንግዶችንና ሠራተኞችን ተቀብሎ ከራሱ ገቢታ ይመግባቸው ነበር።

# ጥያቄዎች ነህምያ 3-7

1. የአሽዶድና የቴቁሐ ሰዎች ከኢየሩሳሌም በየትኛው አቅጣጫ ይኖራሉ?
2. በይሁዳ የነበሩትን አራት መኅበረ ሰባዊ ችግሮች ዘርዝር።
3. በመጀመሪያ ጊዜ ነህምያ በኢየሩሳሌም ውስጥ የቆየው ለስንት ዓመታት ነው?
4. ንጉሥ አርጤክስስ ለነህምያ የሰጠው ሥልጣን ምንድነው?
5. ነህምያ ግንቦቹን ለመገንባት ያቀደበትን ምክንያት በአጭሩ ግለጽ።
6. የግንቦቹ ግንባታ እንዲቆም ጠላቶቻቸው የተጠቀሙባቸው ዘዴዎች ምንድናቸው?
7. ጠላቶቹ የግንባታው ሥራ እንዲቆም ማዘዝ ያልቻሉት ለምን ነበር?
8. ነህምያን ለማታለል የሞከረው ማን ነው? እነማን ቀጠሩት?
9. ነህምያ ወደ ቤተ መቅደሱ ቢገባ ኖሮ ውጤቱ ምን ይሆን ነበር?
10. ነህምያ የጠላቶቹን ተቃውሞ ሊቋቋም የቻለው እንዴት ነው?

# ክፍል ስድስት ሕጉና ስምምነቱ

## ነህምያ 8-10

### የሙሴ የሕግ መጽሐፍ

ብሉይ ኪዳን ውስጥ የመጀመሪያዎቹ አምስት መጽሐፍት እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ለእስራኤል የሰጣቸው የሕግ መጽሐፍት ናቸው። ከነህምያ ዘመን መንግሥት 70 ዓመታት በፊት እስራኤላውያን በምርኮ ተይዘው በየአገሩ ተበታትነው ነበር። የሙሴን ሕግ የሚያውቁ ትልልቅ ሰዎች ሞተው ነበር። በምርኮ ጊዜ አንዳንድ እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ሕጉ እንደሚነበብ ሰሙ። አንዳንዶቹ እስራኤላውያን ምናልባት ይህንኑ አልሰሙም፤ ሕጉንም አላጠኑም። በኢየሩሳሌም ለተሰበሰቡት ለአብዛኞዎቹ የእግዚአብሔር ሕግ አዲስ ነገር ነበር፤ ነህምያ 8፡8-9።

### የዳስ በዓል

እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን እንዲያከብሩ ካዘዛቸው በዓላት አንዱ የዳስ በዓል ነበር። ይህ በዓል የማመስገን በዓል ነው። በዓሉ የሚከናወነው በመኸር ወቅት ነው፤ በእያንዳንዱ ቀን ምስጋናና ለሰብሉ መሥዋዕት ይቀርብ ነበር። ይህም አርባዎቹን የጉዞ ዓመታት ማስታወሻ ጊዜ ነበር። ሕዝቡ ከዛፍ ቅርንጫፍ ዳስ ሠርተው በውስጡ ለሰባት ቀናት ይቀመጡ ነበር፤ ዘፀአት 23፡16፤ ዘሌዋ.23፡34 እና 39-43።

## የነህምያ 8-10 ታሪካዊ አቀማመጥ

በይሁዳ የነበሩት እስራኤላውያን ብዙ ችግሮች ነበሩባቸው። እነዚህ ችግሮቻቸው ለእግዚአብሔር ባለመታዘዝ የመጡ ናቸው። ታላላቅ እስራኤላውያን ሕጉን ሲታዘዙ፥ መሬቶቹን ሲመልሱና ባሪያዎቹን ነፃ ሲለቁ እግዚአብሔር ሊባርካቸው ይችላል። እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ቃል በብዛት ለመስማት ፈለጉ። የፈራረሱትን ቅጥሮች ገነቡ፤ ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱት ሁሉ ተመዝግበው ነበር። ከዚያም ሰዎቹ ወደየከተሞቻቸውና ወደየመንደሮቻቸው ተበተኑ። ቢሆንም የእግዚአብሔርን ቃል መማርና ማወቅ ስለፈለጉ በኢየሩሳሌም ተሰብስበው ዕዝራ እንዲያስተምራቸው ጠየቁት።



## የነህምያ 8-10 ታሪክ

### ዕዝራ ትዕዛዙን ለሕዝቡ አነበበ

ግንቦቹ ተሠርተው ካለቁ በኋላ ሕዝቡ ይሁዳ ውስጥ ወደየከተሞቻቸው ሄዱ። ሆኖም በሰባተኛው ወር በመጀመሪያው ቀን ሕዝቡ እንደገና ኢየሩሳሌም ውስጥ ተሰበሰቡ። ካህኑ ዕዝራ ሕጉን እንዲያነብላቸው ጠየቁት። ከንጋት እስከ ምሽት ካህናቱ ሕጉን ሲያነቡና ሲገልጹ ወንዶች፥ ሴቶችና ሕፃናት ቆመው ያዳምጡ ነበር። ዕዝራ የሕጉን መጽሐፍ ሲከፍት ሕዝቡ ይቆማሉ፤ ከዚያም ለማምለክ ይንበረከካሉ። ቃሉን ለማዳመጥ ለስድስት ሰዓታት ይቆማሉ። ሕጉን ሲሰሙ ማልቀስ ጀመሩ። ነህምያ፥ ዕዝራና ሌዋውያን «ይህ ቀን በእግዚአብሔር ዘንድ የተባረከ ቀን ስለሆነ አታልቅሱ። እቤት ሄዳችሁ በዓል አድርጋችሁ ከሌላቸው ጋር ተካፈሉ። እግዚአብሔር የሰጣችሁ ደስታ ብርታታችሁ ነው» አሉአቸው።

### የዳስ በዓል ተደረገ

የጎሣዎቹ መሪዎች፥ ካህናትና ሌዋውያን ሕጉን ለማጥናት በሁለተኛው ቀን ተሰበሰቡ። የዳስን በዓል በሚያከብሩበት ጊዜ በዳስ ውስጥ እንዲኖሩ እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው ሰሙ። ስለዚህ መሪዎች፥ ካህናትና ሌዋውያን ከከተሞቻቸው ወጥተው ሙሴ በሕግ መጽሐፉ ላይ እንደጻፈው ዳስ እንዲሠሩ አዘዙአቸው። ሕዝቡ ዳስ ሠርተው የበዓሉን ሳምንታት እዚያው አሳለፉ። ከኢያሱ ዘመን መንግሥት ወዲህ ሕዝቡ ዳስ ውስጥ አልተቀመጡም ነበር። በየቀኑ ከእግዚአብሔር ሕግ ያነቡ ነበር። ለሰባት ቀናት ካከበሩ በኋላ እግዚአብሔር እንዳዘዘው በስምንተኛው ቀን በዓሉን ጨረሱ፤ ነህምያ 8፡13-18።

### ሕዝቡ ኃጢአታቸውን ተናዘዙ

በሃያ አራተኛው ቀን ሕዝቡ እንደገና ተሰበሰቡ። ስለ ኃጢአታቸው እንዳዘኑ ለማሳየት ጾሙ፤ ከእንግዳ ሚስቶቻቸው ተለያዩ፤ ማቅ ለብሰው ራሳቸው ላይ አቧራ ነሰነሱ። ከዚያም እነርሱና አባቶቻቸው ስለሠሩት ኃጢአት ተናዘዙ። ሕጉን ለሦስት ሰዓታት ከሰሙ በኋላ እንደገና ለሦስት ሰዓታት ኃጢአታቸውን ተናዘው እግዚአብሔርን አመለኩ፤ ሌዋውያኑም በአምልኮአቸው መሩአቸው።

### የኑዛዜ ጸሎት

ሕዝቡ ኃጢአታቸውን ከተናዘዙ በኋላ ሌዋውያን በታላቅ ጸሎት ሕዝቡን መሩ። ጸሎቱ እግዚአብሔር ታላቅ ፈጣሪ ስለሆነ በምስጋና ይጀርና ከአብርሃም ጊዜ ጀምሮ የነበረውን የእስራኤላውያንን ታሪክ ይናገራል። ሕዝቡን ከግብፅ ለማውጣት እግዚአብሔር ያደረገውን መሰናዶ ይናገራል። ሕዝቡ በእግዚአብሔር ላይ ሲያምጹና በወርቅ ጥጃ ሲያመልኩ እንደነበረ ተናዘዙ። ወደ ተስፋ ምድር ስለመራቸው ስለ ኢያሱና በነቢያትና በመሳፍንት ጊዜ ስለነበራቸው ድከመት ተናገሩ። ከዚያም የራሳቸውን አለመታዘዝና ሌሎች ኃጢአቶችን ተናዘዙ።

እግዚአብሔር እንዲረዳቸው ለመኑ። እነርሱ ኃጢአተኞች መሆናቸውንና እግዚአብሔር ስለቀጣቸው ትክክለኛ እንደሆነና ታማኝ መሆኑን ተናገሩ። አሁንም በራሳቸው መሬት በእንግዳ መሪዎች የሚገዙ ስለሆኑ እግዚአብሔር እንዲያስታውሳቸው በመለመን ጸሎታቸውን ጨረሱ።

### ስምምነቱ

እስራኤላውያን መሪዎች፥ ገዢው፥ ካህናትና ራሳቸውን ከእግዚአብሔር ዘንድ ያገለሉ ሁሉ ስምምነት ለመፍጠር ተስማሙ። ስምምነቱም እነዚህን ያጠቃልላል።

1. ማንም እስራኤላዊ አረመኔ ሚስት ወይም ባል ማግባት አይችልም።
2. ሁሉም የሰንበትን ቀን ያስባሉ።
3. ሰባተኛውን ወይም የሰንበትን ዓመት ያከብራሉ።
4. ለቤተ መቅደሱ ግብር ይከፍላሉ።
5. ለመሠዊያው እንጨት ያመጣሉ።
6. ለካህናቱና ለሌዋውያን አንዳንድ ነገሮችን ይሰጡ ነበር።
7. የእግዚአብሔርን ቤት ችላ አይሉም።

ካህናቱና መሪዎቹ በስምምነቱ ላይ ፈረሙ፤ ነህምያ 10፡28-39።

## ጥያቄዎች ነህምያ 8-10

1. ስለ ሰንበት ዓመት የተሰጠው ሕግ ምንድነው? ዘሌዋውያን 25፡2-7 ተመልከቱ።
መልስ፡- በየሰባተኛው ዓመት መሬቱ ሳይታረስ መተው አለበት።
2. ስምምነቱ ለመሠዊያው እንጨት ማቅረብን ለምን ያጠቃልላል?
መልስ፡- ትዕዛዙ በመሠዊያው ላይ አለማቋረጥ እሳት ማንደድ ስለሆነ፤ ዘሌዋ. 6፡12።

## የእግዚአብሔር የማይለወጥ ቃል

### የእግዚአብሔርን ታማኝነት ማስታወስ

ሌዋውያን በጸሎት በሚመሩቸው ጊዜ ሕዝቡ ከአብርሃም ጊዜ ጀምሮ የነበራቸውን ታሪክ አስታወሱ። ይህ ማስታወሻ እግዚአብሔር ታማኝና የማይለወጥ መሆኑን ያረጋግጣል። እስራኤላውያን ሲታዘዙ እግዚአብሔር ባረካቸው፤ ሕዝቡ ሳይታዘዙ ይሠቃዩ ነበር። የእግዚአብሔር ቃል አይለወጥም።

### አለመታዘዝ በእስራኤላውያን ላይ ምርኩን አስከተለባቸው

እያንዳንዱን የሕይወት ክፍል በሚመለከት በሙሴ አማካኝነት የተሰጠው የእግዚአብሔር ሕግ በጣም ግልፅ ነበር። እንዴት እንደሚያመልኩና እንዴት እርስ በርሳቸው እንደሚኖሩ ትዕዛዝ ይሰጣል። ከአረመኔ ጐረቤቶቻቸው ጋር እንዳይጋቡና አካባቢያቸው ባሉት አምላኮች እንዳያመልኩ ያስጠንቅቃል። ሕዝቡ እነዚህን ትዕዛዛት ስላላከበሩ በግዞት ወደ ባቢሎን



ተወሰዱ። ዕዝራ ሕጉን በሚያነብበት ጊዜ ሕዝቡ የእግዚአብሔር ቃል እንዳልተለወጠ ተገነዘቡ። የምርኮአቸው ምክንያት አለመታዘዝ መሆኑን አወቁ።

## የነህምያ 8-10 ማጠቃለያ

ግንቦች ተሠርተው እንዳለቁ ሕዝቡ ወደ ከተሞቻቸውና ወደ መንደሮቻቸው ተመለሱ። ሆኖም ትንሽ ቆይተው ዕዝራ የእግዚአብሔርን ሕግ እንዲያነብላቸው ለመጠየቅ እንደገና ኢየሩሳሌም ውስጥ ተሰበሰቡ። ሕዝቡም ታሪኩን እንደሰሙ ማምለክ ጀመሩ። አለመታዘዛቸውን ሲገነዘቡ አለቀሱ። ሆኖም ዕዝራ እንዲደሰቱና በዓል አድርገው ከሌላቸው ጋር እንዲካፈሉ ነገራቸው። ከዚያም እስራኤላውያን የዳስ በዓል አከበሩ። ዳስ ሠርተው በአርባዎቹ የመከራ ዓመታት ውስጥ እግዚአብሔር የጠበቃቸውን በማስታወስ ዳሶቹ ውስጥ ተቀመጡ።

እስራኤላውያን ኃጢአታቸውን በመናዘዝ ይጾሙና ይጸልዩ ነበር። ከእንግዳ ሚስቶቻቸው ተለያዩ። ከዚያም ሌዋውያን በታላቅ ጸሎት ይመሩአቸው ነበር። ባለፉት ታሪኮቻቸው እግዚአብሔር ያደረገላቸውን እንክብካቤ አስታወሱ። እግዚአብሔር ስለቀጣቸው ትክክለኛ መሆኑን ተናዘው አሁንም በሌሎች ገዢዎች በራሳቸው መሬት የሚገዙ ስለሆነ እግዚአብሔር እንዲያስባቸው ለመኑ።

## ጥያቄዎች 8-10

1. እስራኤላውያን ከከተሞቻቸው እንደገና ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱት ለምንድነው?
2. ለብዙ እስራኤላውያን የእግዚአብሔር ቃል አዲስ የነበረው ለምንድነው?
3. የዳስን በዓል ያከበሩበት ምክንያት ምንድነው?
4. የዳስ በዓል የምስጋና በዓል ነው። ምስጋና ያቀረቡበት ሁለት ምክንያቶች ምንድናቸው?
5. ሕጉ በሚነብበበት ጊዜ ሕዝቡ የሚያለቅሱት ለምን ነበር?
6. ባለፉት የሕይወት ዘመናት እግዚአብሔር ያደረገልንን ማስታወስ ለምን ይጠቅማል?
7. የእስራኤላውያን መሪዎች በስምምነቱ ላይ የጨመሩአቸውን ሰባቱን ነገሮች ተመልከቱ።
8. መሬቱ በሰባተኛው ዓመት የማይታረሰው ለምን ነበር?
9. እስራኤላውያን በግዞት እንዲያዙ ያደረጉትን ሦስት ኃጢአቶች ጥቀስ።
10. በአሁኑ ጊዜ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ አለመታዘዝ ካለ የሚያደርገው ነገር አለ? እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚቀጣባቸው መንገዶች ምንድናቸው? በክርስቲያኖች ውስጥ ባለመታዘዝ ያሉት ኃጢአቶች ምንድናቸው?

# ክፍል ሰባት የነህምያ ሥራ

## ነህምያ 11-13

ነህምያ በገዢነት ለአሥራ ሁለት ዓመታት በኢየሩሳሌም ቆየ። በአሥራ ሁለተኛው ዓመት ወደ ፋርስ ተመለሰ፤ ነህምያ 13፡6። መቼ ወደ ኢየሩሳሌም እንደተመለሰ ወይም ለምን ያህል ጊዜ በገዢነቱ እንደቀጠለ እርግጠኛ ማስረጃ የለም፤ ሆኖም ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሷል፤ ነህምያ 13፡6-7።

## የነህምያ 11-13 ታሪካዊ አቀማመጥ

ኢየሩሳሌም የእስራኤላውያን ዋና ከተማና ቅድስት ከተማ ነበረች። እስራኤላውያን ከባቢሎን ምርኮአቸው ወደ አገራቸው ሲመለሱ የሄዱት ወደ ኢየሩሳሌም ነበር። ቢሆንም የከተማዋ ግንቦች ፈራርሰው ስለነበረ ለመኖር አመቺ አልነበረችም። ስለዚህ ብዙ እስራኤላውያን በይሁዳ ባሉ ሌሎች ከተሞች ውስጥ ሠፈሩ። ከተማዋን የሚጠብቁና የሚኖሩባት በቂ ሰዎች አልተገኙም። ነህምያ 7፡4 እንዲህ ይላል፦ «ኢየሩሳሌም ትልቅ ከተማ ናት፤ ነገር ግን ብዙ ሰዎች አይኖሩባትም።»

## የነህምያ ታሪክ 11-13

### የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች

የኢየሩሳሌም ቅጥሮች ተሠርተው አለቁ። ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቃል ሲሰሙ ስለ ኃጢአታቸው ተወቀሱ። ኃጢአቶቻቸውን ተናዘው በሕይወታቸው ትክክለኛውን ነገር ማድረግ ጀመሩ። ነህምያ ከተማዋን ለመሥራት እቅድ አቀደ። በመጀመሪያ ብዙ እስራኤላውያን ወደ ኢየሩሳሌም መመለስ ነበረባቸው። አንዳንዶች በፈቃደኝነት ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ሲነሡ ሌሎች በዕጣ ተመርጠው ሄዱ። ከአሥር ቤተሰብ አንዱ ተመርጦ በኢየሩሳሌም እንዲኖር ተደረገ። ሌሎች በይሁዳ ውስጥ ባሉ ሌሎች ከተሞችና መንደሮች ይኖሩ ነበር።

### በኢየሩሳሌም የሚኖሩት ዝርዝር

በዚያን ጊዜ በኢየሩሳሌም የሚኖሩት ዋና ዋና ቤተሰቦች በነህምያ 11፡3-19 ውስጥ ተመዝግበዋል። ከቁጥር 20-24 ውስጥ ሌሎች በከተማው የሚኖሩ ሰዎች ተመዝግበዋል።



### በይሁዳ ያሉት ከተሞች

ብዙዎቹ እስራኤላውያን የሚኖሩት መሬቶቻቸው አካባቢ ባሉ ከተሞች ነበር። እነዚህ ከተሞችና መንደሮች በነህምያ 11፡25-35 ውስጥ ተመዝግበዋል። ነህምያ 11ን አንብቡ።






## አስፈላጊ ዝርዝሮች

የመጀመሪያው ዝርዝር ከዘሩባቤል ጋር ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱት የካህናቱና የሌዋውያን ቤተሰቦች ዝርዝር ነበር። እነዚህ የሃይማኖት መሪዎች ነበሩ። እንደ እግዚአብሔር ሕግ መሠረት እያንዳንዳቸው ከትክክለኛ ጎሣ መሆን ነበረባቸው፤ ነህምያ 12፡1-9።

ሁለተኛው መዝገብ ከኢያሱ ዘመን ጀምረው የነበሩት የታላላቅ ካህናት መዝገብ ነበር፤ ነህምያ 12፡10-11።

ሦስተኛው ዝርዝር በዮአቂም ዘመን የነበሩት የካህናት አለቆች ዝርዝር ነበር፤ ነህምያ 12፡12-21።

በመጨረሻም በኤልያሴብ፥ በዮአዳ፥ በዮናታንና በያዱአ ዘመን የነበሩት የካህናትና የሌዋውያን አለቆች ዝርዝር ነበር። ምዝገባው ዳርዮስ የፋርስ ንጉሥ ሲሆን ተፈፀመ። የሌዋውያን መዝገብ ከዮአቂም ዘመን እስከ ነህምያና ዕዝራ ዘመን ተጻፈ፤ ነህምያ 12፡22-26።



## ግንቦቹ ተመረቁ

ግንቦቹ ከተሠሩ በኋላ በአምልኮ ሥነ ሥርዓት ተመረቁ። ብዙ ዘማሪዎች በምስጋና ይዘምሩ ነበር። ካህናቱና ሌዋውያን ራሳቸውን፥ ቅጥሮቹን፥ መግቢያዎቹንና ሕዝቡን አነጹ። ይህ የተደረገው የኃጢአትና የሚቃጠሉ መሥዋዕቶችን በማቅረብ ሳይሆን አልቀረም፤ 2ኛ ዜና 29፡29።

ቀጥሎም ነህምያ ሕዝቡን በሁለት ቡድን ከፋፈለ። አንዱ ቡድን በዕዝራ እየተመራ ከደቡባዊ ግንብ ወደ ምሥራቃዊው ግንብ ተጓዘ። ሌላው ቡድን በነህምያ እየተመራ ከሰሜናዊው ግንብ ወደ ምሥራቃዊው ግንብ ተጓዘ። እዚያም ሁለቱ ቡድኖች ተገናኝተው ወደ ቤተ መቅደሱ በመሄድ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቀረቡ። ታላቅ ደስታ ስለነበረ የሕዝቡ መዝሙርና ምስጋና ከሩቅ ይሰማ ነበር፤ ነህምያ 12፡27-43።






## ለቤተ መቅደሱ ሥጦታና መሥዋዕት ተሰበሰበ

የሚቀርቡትን ሥጦታዎችና መሥዋዕት የሚሰባስቡ ሰዎች ተመረጡ። በመጀመሪያ የሚደርሱት በቆሎና ፍራፍሬ በየዓመቱ ያከማቹ ነበር። ሕዝቡ የቤተ መቅደሱን ዘማሪዎችና ጠባቂዎች ለመቀበል ሥጦታ ይሰጡ ነበር። በተራቸው ለሚሰጡት ለካህናትና ለሌዋውያን ሥጦታ ይሰጡ ነበር፤ ነህምያ 12፡44-47።

## ነህምያ ከፋርስ ተመለሰ

የግንቡ ሥራ ከማለቁ በፊት እንኳን ነህምያ ወደ ሱሳ ለመመለስ አስቦ ነበር። ሥራው ካለቀ በኋላ ቢመለስም በኢየሩሳሌም የቆየበት ጊዜ አልታወቀም። ነህምያ 13፡6 ላይ ነህምያ ወደ ፋርስ መሄዱን ይናገራል፤ ነገር ግን ወደ ኢየሩሳሌም ለመመለስ ከንጉሥ አርጤክስስ እንደገና ፈቃድ ተቀበለ።

ነህምያ ፋርስ ውስጥ እያለ የቤተ መቅደሱን ማከማቻ ክፍል እንዲጠብቅ የተመረጠው ካህን ከማከማቻ ክፍሎቹ ትልቁን እንዲወስድ ለጦብያ ፈቃድ ሰጠው። ነህምያ ተመልሶ ይህንን በማየቱ በጣም ተቆጣ። ጦብያንና ዕቃዎቹን ከቤተ መቅደሱ አስወጣ። የቤተ መቅደሱ ክፍሎች እንዲፀዱና ጥራጥሬዎቹና ዕቃዎቹ ወደ ቤተ መቅደሱ እንዲመለሱ አዘዘ።



## ነህምያ ያሻሻላቸው ሌሎች ነገሮች

ሕዝቡ ለቤተ መቅደሱ ይሰጡት የነበረውን ሁሉ በማቆማቸው ዘማሪዎቹና ሌዋውያን ኢየሩሳሌምን ትተው ወደ ግብርናቸው ተመለሱ። ነህምያ ወደ ቤተ መቅደሱ መልሶአቸው የቤተ መቅደሱን ባለሥልጣኖች ሰብስቦ ሥራቸውን ችላ ስላሉ ገሠጻቸው።

ሕዝቡ በሰንበት ቀን ለመሸጥ የተለያዩ ዕቃዎችን ወደ ኢየሩሳሌም ያመጡ ጀመር። የሰንበትን ቀን ስላረከሱ ነህምያ እስራኤላዊ መሪዎችን ገሠጸ። «አባቶቻችሁ ይህንን ስላደረጉ ነው እግዚአብሔር የቀጣቸው» አላቸው።

በሰንበት ቀናት የከተማዋ በሮች እንዲዘጉ ነህምያ አዘዘ። ማንም ዕቃ ወደ ከተማው እንዳያስገባ በየመግቢያዎቹ ላይ ጠባቂዎች አስቀመጠ። ሌዋውያን ራሳቸውን አንፅተው የሰንበት ቀን የተቀደሰ ሆኖ እንዲውል በየበሮቹ ላይ እንዲቆሙ ነገራቸው።

ብዙ እስራኤላውያን እንደገና ለእግዚአብሔር ቃል ሳይታዘዙ ከአሞን፣ ከአሽዶድና ከሞአብ ሴቶች ጋር ተጋቡ። እንደገና ከአንግዳ ሴቶች ጋር እንዳይጋቡ እንዲምሉ ነህምያ አስገደዳቸው። ይህ የሰለሞን ኃጢአት መሆኑን አስታወሳቸው። የዩአዳ ልጅ የሰንባላጥን ልጅ ስላገባ ከኢየሩሳሌም እንዲወጣ ነህምያ አደረገው። ነህምያ ወደ ፋርስ ከመመለሱ በፊት ያስተካከላቸውን ነገሮች ሁሉ ሕዝቡ እንደገና ማድረግ ጀመሩ።

# ጥያቄዎች ነህምያ 11-13

1. ቤቶቹን፣ መሠውያውን ወዘተ ማንጻት ለምን አስፈለገ?

መልስ፡- በአረት ዘመን እንደ ቤት የመሳሰሉ ሕይወት የሌላቸው ነገሮች እንኳን ሊረከሱ ይችላሉ፤ ዘዳግም 23፡14፤ ዘሌዋ.14፡34-53 እና 16፡16።

2. ነህምያ አንዳንድ ነገሮች ስላስተካከለ እግዚአብሔር ይጠብቀኛል ብሎ አስቦ ነበር? ነህምያ 13፡14፤22 እና 29።

መልስ፡- አላሰበም። ነህምያ እግዚአብሔር መሐሪ አምላክ ስለሆነ እንዲረዳው ጠየቀ። ገዢ ስለነበር ስለ ሕዝቡ ኃላፊነት ይሰማው ነበር።

3. ሰንበት የሚጀምረው መቼ ነበር? ነህምያ 13፡19።

መልስ፡- ሰንበት የሚጀምረው ከዓርብ ምሽት ጀምሮ እስከ ቅዳሜ ምሽት ነበር።

# የእግዚአብሔር የማይለወጥ ቃል

የሕዝቡ ታዛዥ አለመሆን አባቶቻቸው ላይ ቅጣት እንዳመጣባቸው አሁንም በነህምያ ጊዜ ቁጣት ያመጣል። የሰንበትን ቀን በማርከሳቸው አባቶቻቸው ተቀጥተው እንደነበር ነህምያ ሕዝቡን አስታወሳቸው፤ ነህምያ 13፡17-18። ሰለሞን እንግዳ ሚስት በማግባቱ ኃጢአተኛ እንደነበረና እነርሱም ከአንግዳ ሚስቶቻቸው ጋር እንዲፋቱ ነገራቸው፤ ነህምያ 13፡26-27።

# ማጠቃለያ ነህምያ 11-13

ነህምያ ጠንካራና ደፋር መሪ ነበር። መሪነቱም በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት ላይ የተመሠረተ ነበር። በጸሎት የኢየሩሳሌም ግንቦች ተገነቡ፤ በጸሎት ነህምያ ያለ ፍርሃት የሕዝቡን የሌዋውያንንና የካህናቱንም ኃጢአት ፈረደ። በጸሎትና በምስጋና የከተማዋ ግንቦች ለእግዚአብሔር ክብር ተሠሩ። ነህምያ ከፋርስ ሲመለስ ከዚህ በፊት ፍርድ ሰጥቶባቸው የነበረውን በካህናቱ፣ በሌዋውያኑና በሕዝቡ ኃጢአት ላይ እንደገና ፍርድ መስጠት ነበረበት። በዚህ ሁሉ ሥራ ነህምያ የእግዚአብሔርን ምሕረት ይለምን ነበር። እግዚአብሔር ነህምያን ባርኮ ሕዝቡን ወደ ተስፋው ምድር እንዲመራ አደረገው።

# ጥያቄዎች ነህምያ 11-13

1. ነህምያ ወደ ፋርስ ከመመለሱ በፊት ኢየሩሳሌም ውስጥ ለስንት ዓመት ቆየ? ስለመመለሱ የሚናገሩት ቁጥሮች የትኞቹ ናቸው?
2. ብዙ ሰዎች ኢየሩሳሌም ውስጥ እንዲኖሩ ነህምያ የፈለገው ለንምድነው?
3. ነህምያ ኢየሩሳሌም ውስጥ ሰዎች እንዲኖሩ ያደረገው እንዴት ነበር?
4. የካህናቱ፣ የሌዋውያኑና የዋና ዋና ቤተሰቦች ዝርዝር የመንግሥት መዝገብ ላይ የተመዘገቡት ለምንድነው?
5. ግንቦቹ እንዴት እንደተመረቁ ግለጽ።
6. እጅ መንሻዎቹና ሥጦታዎቹ የሚሰበሰቡት ለምን ነበር?
7. ጦብያ የእግዚአብሔርን ሥራ ሊያደናቅፍ የቻለው በምን መንገድ ነበር?
8. ብዙ እስራኤላውያን ሰንበትን ያረከሱት እንዴት ነበር?
9. ብዙዎቹ እስራኤላውያን እየሠሩት የነበረው የሰለሞን ኃጢአት ምን ነበር?
10. ነህምያ በመሪነቱ ብርታት የሚያገኘው ከየት ነበር?



## የመጽሐፈ ነህምያ ንድፍ

የነህምያ
መመለስ
1 - 2

የቅጥሩን
እንደገና
መገንባት
3 - 6

መ ረ ጃ
ጽ ሑ ፍ
7

የእግዚአብሔር
ሕግ መነበብ
8 - 10

የነህምያ
አስተማሪነት
11 - 13

## የመጽሐፈ ዕዝራ ንድፍ

| | | |
|---|---|---|
| 536 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት | 458 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት | 444 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት |

ዕዝራ 1፡1 - 2፡70

በመጀመሪያ የወሰዳቸው እርምጃዎች

3፡1 - 4፡5

ተቃውሞ
4:6-23

የከተማይቱ

የመጀመሪያው እድሳት

4፡24 - 6፡22

የዕዝራ መመለስ

7፡1 - 8፡36

ድብልቅ ጋብቻ

9 - 10



## መልሶች

### ዕዝራ 1-2

1. እስራኤላውያን እግዚአብሔርን አለመታዘዝና ጣዖትን ማምለክ ቀጠሉ።
2. ሰሜናዊው የእስራኤል ግዛት መጀመሪያ ተያዘ። ሕዝቡ ወደ እሥር በግዞት ተወሰዱ።
3. የደቡባዊው እስራኤል ሕዝቦች በግዞት ወደ ባቢሎን ተወሰዱ።
4. የኢየሩሳሌም ከተማ ፈራረሰች፥ ቤተ መቅደሷም ተቃጠለ።
5. ነቢዩ ኤርምያስ በሰባ ዓመት ውስጥ እስራኤላውያን ወደ አገራቸው እንደሚመለሱ ተነበየ።
6. ቂሮስ አሦርንና ባቢሎንን የሚጠቃልለውን የፋርስ ንጉሥ ሆነ። እሱም አረመኔና በእግዚ አብሔር የማያምን ነበር።
7. እስራኤላውያን ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ለመፍቀድ እግዚአብሔር የቂሮስን ልብ አነሣሣ።
8. እስራኤላውያን ኢየሩሳሌም ውስጥ የነበረውን ቤተ መቅደስ መገንባት ነበረባቸው።
9. ያልተመለሱት ሰዎች ብር፥ ወርቅ፥ ዕቃዎችና እንስሳትን ይዘው የሄዱትን መርዳት ነበረ ባቸው።
10. ናቡከደነፆር ከቤተ መቅደሱ ወስዷቸው የነበሩትን የወርቅና የብር ሰሐኖች ቂሮስ መለሰላቸው።

### ዕዝራ 3-6

1. እስራኤላውያን በመጀመሪያ ያደረጉት ኢየሩሳሌም ውስጥ ተሰብስበው መሠዊያውን መገንባትና ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ማቅረብ ነበር።
2. ኢየሩሳሌምና ቤተ መቅደሱ በሚገነቡበት ጊዜ ሐጌና ዘካርያስ ነቢያት ነበሩ፤ ዕዝራ 5፡1 እና 6፡14።
3. የቤተ መቅደሱ ሥራ ለአሥራ ስድስት ዓመታት ተቋረጠ።
4. የፋርስ ነገሥታት፥ ቂሮስ ቀጥሎም ዳርዮስ እስራኤላውያን ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው ቤተ መቅደሱን እንዲገነቡ ረዷቸው።
5. በባቢሎን ስለ ቀሩት እስራኤላውያን የተገኘው ጽሑፍ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው የአስቴር ታሪክ ብቻ ነው።
6. እስራኤላውያን ለቤተ መቅደሱ ሥራ ሥጦታዎችን ያመጡ ነበር። አንዳንዶቹ ሥጦታዎ ቻቸው ከሊባኖስ ለሚመጣው የጥድ እንጨት ይለወጡ ነበር።
7. የእስራኤላውያን ጠላቶች የአገሩ ሕዝብ ነበሩ። በቤተ መቅደሱ ሥራ ላይ ለመካፈል ሲነሡ ዘሩባቤል መጥፎ ሥራ ሊሠሩ እንዳቀዱ አወቀ። ከዚያም እስራኤላውያንን ማስፈራራት ጀመሩ። በመጨረሻም ለፋርስ ገዢዎች የሐሰት ሪፖርት ጻፉ። ገዢዎቹም ሥራውን አስቆሙ።
8. የቤተ መቅደሱ ሥራ እንዲፈጸም ትዕዛዝ እንዲሰጥ እግዚአብሔር ንጉሥ ዳርዮስን አስነሣ።

